# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን የቅርስ ጥናትና ጥበቃን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ጥር 2003 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# ማውጫ


**ክፍል አንድ** .................................................... 1

**መግቢያ** .................................................... 1

*የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን አመሠራረት* .................................................... *2*
*የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር* .................................................... *3*
*የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል* .................................................... *4*
*የባለሥልጣኑ የፋይናንስ ምንጭ* .................................................... *5*
የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ .................................................... 5
የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ .................................................... 6
የኦዲቱ አካባቢ (AUDIT AREA) .................................................... 6
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (AUDIT ISSUES) .................................................... 6
የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (EVALUATIVE CRITERIA) .................................................... 7
የቅርስ ጥናትና ጥበቃ የሥራ ሂደት መግለጫ (PROCESS DISCRIPTION) .................................................... 7

**ክፍል ሁለት** .................................................... 9

ግኝቶች .................................................... 9
*I. የቅርስ ምዝገባን በተመለከተ* .................................................... *9*
የቅርሶች ምዝገባ የሚሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ መመሪያ መዘጋጀቱን በተመለከተ .................................................... 9
ተንቀሳቃሽና ቋሚ ቅርሶች በቦታ ተለይተው ምዝገባ የተደረገላቸው መሆኑን በተመለከተ .................................................... 10
የማይዳሰሱ ቅርሶች ምዝገባ በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተከናወነ መሆኑን በተመለከተ .................................................... 12
የቅርስን ምዝገባ የሚያደርጉ ባለሙያዎች ሙያው የሚጠይቀው ክህሎት እና ሥነ ምግባር ያላቸው መሆኑን በተመለከተ .................................................... 13
ባለሥልጣኑ ለአርኪዮሎጂ ጥናት የሚውሉ ቦታዎችን ለይቶ ምዝገባ ማድረጉን በተመለከተ .................................................... 14
*II. የቅርስ ጥገናና እንክብካቤን በተመለከተ* .................................................... *15*
የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ተግባር መስፈርቱን በጠበቀ መልኩ የሚከናወን መሆኑን በተመለከተ .................................................... 15
ለቅርስ ጥገና እና እንክብካቤ ዙሪያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ የሚሰጥ መሆኑን በተመለከተ .................................................... 17
ለቅርስ ጥገና እና እንክብካቤ ሥራ የሚረዱ የተለያዩ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች መዘጋጀትን በተመለከተ .................................................... 19
ከባለሥልጣኑ እውቅናና ፈቃድ ውጪ ቅርሶች ላይ ጥገናና እንክብካቤ ሲደረግ ህጋዊ እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ .................................................... 20
*III. የቅርስ አጠባበቅና አያያዝን በተመለከተ* .................................................... *23*
ለቅርስ አጠባበቅ ትኩረት መሰጠቱን በተመለከተ .................................................... 23
የቅርስ አስተዳደር ሰነድ (Heritage Managment plan) መዘጋጀቱን በተመለከተ .................................................... 27
በስጦታ መልክ ቅርሶች ወደ ውጪ ሀገር እንዳይሄዱ መከታተልን በተመለከተ .................................................... 31
የአርኪዮሎጂ ጥናት ከሚያደረጉ አጥኚ ቡድኖች ጋር ከባለሥልጣኑ የሚላኩ ባለሙያዎች የመምረጪያ መሥፈርትን በተመለከተ .................................................... 32
በቅርስ ላይ ጥናትና ምርምር ከሚያከናውኑ ባለሙያዎች የሚገኘው ገቢ ለቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ የሚውል መሆኑን በተመለከተ .................................................... 33
ባለሥልጣኑ መ/ቤት እና በፌዴራል ደረጃ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የሥራ ድርሻ በግልጽ ተለይቶ መቀመጡን በተመለከተ .................................................... 34
በቅርሶች አመዘጋገብ፣ አጠባበቅ እና ጥገና ዙሪያ የባለሥልጣኑ እና የክልሎች የሥራ ድርሻ በግልፅ መቀመጡን በተመለከተ .................................................... 35
ቅርስን በመጠበቅ ተግባር የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በጋራ እቅድ በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ .................................................... 37
ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ መ/ቤቶች ተቀናጅተው የሚሠሩበት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ .................................................... 38
በባለሥልጣኑ ለክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች በቅርስ ዙሪያ የሚያደርገውን የሙያ ድጋፍ በተመለከተ .................................................... 39
በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ሊጠበቁ የሚገባቸው ቅርሶች ደረጃ ማውጣትን በተመለከተ .................................................... 42
የልማት ሥራዎች በሚከናወኑበት ወቅት በቅርሶች ላይ ጉዳት እና ጥፋት እንዳይደርስ የማዳን ሥራ የሚከናወን መሆኑን በተመለከተ .................................................... 43
የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች የሥነ ምግባር ደንብን በተመለከተ .................................................... 44

የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ሥራ ለማከናወን  አስፈላጊ ባለሙያ መመደቡን በተመለከተ ..... 45
የተመዘገቡ ተንቀሳቃሽና ቋሚ ቅርሶች የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን በተመለከተ ..... 46
በባለሥልጣኑ የቅርስ ምዝገባን ሥራ በማዕከል ደረጃ በዳታ ቤዝ የተያዘና ከክልሎች ጋር በኔትወርክ የተገናኘ መሆኑን በተመለከተ ..... 47
የቅርስ መረጃዎችን በድረ ገጽ እና በተለያዩ ማሰራጫ መንገዶች ለማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ ..... 48
በባለሥልጣኑና በሁሉም ባለድርሻ አካላት መካከል የቅርስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ ..... 49

**ክፍል ሦስት ..... 51**

መደምደሚያ ..... 51

**ክፍል አራት ..... 53**

የማሻሻያ ሀሳቦች ..... 53

**አባሪ ..... I**

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ቅርስ ማለት በቅድመ ታሪክና በታሪክ ዘመን የሰው ልጅ የፈጠራና የሥራ እንቅስቃሴ ውጤት የሆነ የተፈጥሮ የለውጥ ሂደትን የሚገልጽና የሚመሰክር በሳይንስ፤ በታሪክ፤ በባህል፤ በሥነ ጥበብና በእደጥበብ ይዘቱ ከፍተኛ ተፈላጊና ዋጋ ያለው ሀብት ሲሆን፣ ይህም ሀብት የሚዳሰስ (tangible) እና የማይዳሰስ (intangible) በሚል ይከፈላል፡፡ ግዙፍነት ያላቸው ቅርሶች ማለት በእጅ የሚዳሰሱ እና በአይን የሚታዩ ቅርሶችን የሚያካትት ሲሆን፣ የሚንቀሳቀሱ እና የማይንቀሳቀሱ ባህላዊና ታሪካዊ ወይም ሰው ሠራሽ ቅርሶችን ይጨምራል፡፡ ግዙፍነት የሌላቸው ቅርሶች ማለት በእጅ ለመዳሰስ የሚያዳግቱ ነገር ግን በአይን ለማየት በጆሮ ለመስማት የሚቻሉ ቅርሶችን ሲሆኑ፣ የብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ልዩ ልዩ ትርዒቶች፣ ጨዋታዎች እና ስነቃሎች እንዲሁም የሃይማኖት፣ የእምነት፣ የጋብቻ እና የሀዘን ሁኔታዎች የሚገለጹባቸው ሥነ ሥርዓቶች፤ ሙዚቃዎች፣ ድራማ ሌሎች ተመሳሳይ ባህለዊ እሴቶች፣ ወግና ልማዶችን ይጨምራል፡፡

2. የተለያዩ ሀገራት የተለያየ አይነት እና መጠን ያለው ቅርስ ያላቸው ሲሆን፣ ሀገራችንም እጅግ ከፍተኛ ዋጋ እና ቦታ የሚሰጣቸው እንደ አክሱም፣ ላሊበላ፣ ጎንደር ዙሪያ እና ሀረር ታሪካዊ ቦታዎች፤ እንደ ሰሜን እና ባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርኮች፣ ሶፍዑመር ዋሻ፣ የጣና ደሴቶችና ዙሪያ፣ የኮንሶ አካባቢን የመሳሰሉ ውብ የተፈጥሮ አካባቢዎች እና ብርቅዬ የሆኑ እና የሀገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦች አኗኗር የሚያንጸባርቁ ባህላዊ ቅርሶች ባለቤት ነች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሰው ዘር አመጣጥ እና ሂደትን የሚያሳዩ መረጃዎች ምንጭ የሆኑ ድንቅ አርኪዎሎጂ ቦታዎች የሚገኙባት ሀገር ናት፡፡ ከነዚህም ውስጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተያዙ ስምንት ቅርሶች ያሏት ሲሆን፣ እነሱም የጥያ ትክል ድንጋዮች፤ የኦሞ ሸለቆ የፓሊዮንቶሎጂ እና ቅድመ ታሪክ ሳይት፤ በጎንደር ፋሲል ግቢ ውስጥ የሚገኙ ግብረ ህንፃ እና ቤተ መንግስቶች፤ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፤ ጥንታዊ የሀረር ግንብ፤

የአክሱም ሀውልቶች፣ የሰሜን ተራራ ብሄራዊ ፓርክ (የተፈጥሮ ቅርስ) እና የታችኛው አዋሽ ሸለቆ የፓሊዮንቶሎጂና ቅድመ ታሪክ ሳይት ናቸው፡፡

3. የአንድ ሀገር መለያ እና መገለጫ የሆኑ ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና የተፈጥሮ ቅርሶች ባሉበት ሁኔታ ተጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ውስብስብ እና አስቸጋሪ የሚያደርጉት ሁኔታዎች ያሉ ሲሆን፣ ከነዚህ መካከልም የተለያዩ ባለድርሻዎችን ተሳትፎ መጠየቁ፣ የቆዩበት ዘመን ርዝመት፣ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ የዓለም አቀፋዊነት (globalization) ተጽዕኖ እየጎላ መምጣት፣ ወዘተ… በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

4. በቅርሶች ላይ እየደረሰ ያለውን ጉዳት ለመከላከል ከአንድ ሀገር አቅም በላይ ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት እና ቅርሶች በባለቤትነት ለያዛቸው ኅብረተሰብ ብቻ ሳይሆን ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብም ያላቸውን የጎላ ጠቀሜታ በመገንዘብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከአራት አስርተ ዓመታት በፊት እ.አ.አ በ1972 ዓ.ም. ዓለም አቀፍ ስምምነት ተደረሷል፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም ይህን ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ ከፈረሙ ሀገሮች መካከል አንዷ ነች፡፡

5. በመሆኑም ይህንን በልዩነት የሚታየውን የሀገሪቷን ልዩ ገጽታ (Identity) የሚያሳዩ ታሪካዊ፣ ተፈጥሮአዊ እና ባሕላዊ ቅርሶች ይዘታቸውን ሳይለቁ ባሉበት ሁኔታ፤ የትኛውም ሌላውን ሳይጫን እና መበላለጥ ሳይታይበት ቀድሞ የነበረው ትውልድ ሲጠብቃቸው እንደነበረው የአሁኑም ሆነ መጪው ትውልድ እንዲይዛቸው እና ከትውልድ ወደ ትውልድ ተጠብቀው እንዲሸጋገሩ እንዲሁም በሀገሪቱ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥም የድርሻቸውን እንዲያበረክቱ አቅም የፈቀደውን ያህል ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

## የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን አመሠራረት

6. ቀደም ሲል ከ1940ዎቹ ጀምሮ የሀገሪቱን ቅርሶች ለመጠበቅ ጥረት ሲደረግ የቆየ መሆኑን ከተለያዩ መረጃዎች ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ በ1945 ዓ.ም. ተጠሪነቱ ለጽህፈት ሚኒስቴር ሆኖ ኢንስቲትዩት አርኪዎሎጂ የተባለ ተቋም በፈረንሳይ መንግሥት ትብብር መቋቋሙ እና በ1958 ዓ.ም. የመዋቅር ለውጥ በማድረግ "የጥንታዊ ቅርሶች አስተዳደር" ተብሎ ራሱን ችሎ በቦርድ እንዲተዳደር በአዋጅ

ቁጥር 45/1958 ዓ.ም. መደራጀቱ፤ በ1968 ዓ.ም. በባህል፤ ስፖርትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ስር "የጥንታዊ ቅርሶች አስተዳደር" የቅርስ ጥናትና ጥበቃ መምሪያ" ተብሎ እንዲዋቀር መደረጉ፤ በ1987 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 4/87 ቀደም ሲል የነበረውን የባህል፤ ስፖርት እና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርን ስያሜና አወቃቀር በመለወጥ የባህል እና ማስታወቂያ ሚኒስቴር ተብሎ ሲዋቀር የቅርስ ጥናትና ጥበቃ መምሪያ ወደ "የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ድርጅት" ከፍ ብሎ መዋቀሩ እንዲሁም ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ ይህ ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 209/92 ተጠሪነቱ ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እንዲሆን በማድረግ በባለሥልጣን ደረጃ ተዋቅሮ በቅርስ ዙሪያ የሚከናወኑ ተግባራትን እንዲያከናውን መደረጉ የሀገሪቱን ቅርስ ለመጠበቅ በተለያየ ጊዜ ከተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

# የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር

7. የባለስልጣን መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፑቢሊክ አስፈጻሚ አከላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 209/1992 ዓ.ም. እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፡፡

- ቅርሶችን ይንከባከባል፤ ይቆጣጠራል፤ እንዲሁም ስለቅርሶች መረጃ ይሰበስባል፤ ቅርስ መሆን ያለመሆኑን ይለያል፤ ደረጃም ያወጣል፡፡ እንዲሁም አግባብ ካለው አካል ጋር በመተባበር ቅርሶችን ይመዘግባል፡፡
- ስለቅርስ ምንነት ጥቅምና አጠባበቅ አስፈላጊው ትምህርትና ምክር ይሰጣል፡፡ ባለስልጣኑ የተቋቋመበትን አላማ ለማስፈፀም ባለሙያዎች በመስኩ እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፡፡
- ቅርሶችን በሙዚየም በማሰባሰብ ለጐብኚዎችና ለተመርማሪዎች ያቀርባል በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ኢግዚቢሽን በማዘጋጀት እንዲታይ ያደረጋል፡፡
- በቅርሶች ላይ ጥናትና ምርምር፤ ጥገናና እንክብካቤ ሥራዎች ይሰራል፡፡ ፈቃድ ይሰጣል ይቆጣጠራል፡፡ እንዲሁም ለየክልል መስተዳድሮች የሙያና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

- ቅርሶች ከሀገር እንዳይወጡ ይቆጣጠራል በልዩ ልዩ ህገወጥ በሆኑ መንገዶች ተወስደው በውጭ ሐገር የሚገኙ ቅርሶች ወደ ሐገር የሚመለሱበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡

- በስጦታ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄዱ ዕቃዎች ቅርስ አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዐት ይዘረጋል፡፡ ለጥናትና ለምርምር ወደ ውጭ ለሚላኩ የአርኪዎሎጂ ናሙናዎች ካስቶች ፈቃድ ይሰጣል፡፡ ለንግድ አላማም እንዳይውሉ አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

- ቅርሶችን በተመለከተ ሀገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

- በአለም አቀፍ፤ በአገርና በክልል ደረጃ ኢትዮጵያን በተመለከተ የሚቀርቡ ቅርስ ነክ የሆኑ ኢግዚቢሽኖችን ደረጃ ያወጣል፤ ፈቃድ ይሰጣል፡፡ለሚሰጠው ፈቃድና አገልግሎት ያስከፍላል፡፡

- በታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ስያሜና ምስል የሚወጡ የንግድና ሌላም ምልክቶች የቅርስን ታሪካዊ እሴት የማይጎዱ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

## የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል

8. የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ተጠሪነቱ ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሆኖ በአንድ ዋና ዳይሬክተር እና በአሥራ ሦስት ዳይሬክቶሬቶች የተዋቀረ ሲሆን፣ ከነዚህም ስድስቱ ዳይሬክቶሬቶች ባለስልጣኑ የተቋቋመበትን ዐብይ ዓላማ ዋና አስፈፃሚ ሲሆኑ፣ የተቀሩት ሰባቱ ደግሞ ድጋፍ ሰጪ ናቸው፡፡ በ2002 በጀት ዓመት በባለሥልጣኑ በተደረገው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት ኃላፊነቱን ለመወጣት 225 የሰው ኃይል እንደሚያስፈልገው የተቀመጠ ሲሆን፣ ይህ ኦዲት በተከናወነበት ወቅት በባለስልጣኑ ያለው የሰው ኃይል ብዛት 202 እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

9. ከዚህም ሌላ ባለስልጣኑ የተሰጠውን የሥራ ኃላፊነት ለመወጣት ከተለያዩ የባለድርሻ አካላት ማለትም ከዩኔስኮ-United Nation Educational, Scientific and Cultural Organization (UNESCO)፤ ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት

ሚኒስቴር፣ ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች እና ከትምህርትና የምርምር ተkማት ወዘተ... ጋር የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፡፡

## የባለሥልጣኑ የፋይናንስ ምንጭ

10. የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ሥራውን የሚያከናውነው ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት እና ከተለያዩ አገልግሎቶች እና ከፈቃድ ከሚሰበሰብ ገቢ ነው፡፡ ባለስልጣኑ ባለፉት ሦስት ተከታታይ የበጀት ዓመታት ማለትም በ1999፤ በ2000 እና በ2001 እንደ ቅደም ተከተሉ ለመደበኛ በጀት ብር 14.07፤ 8.26 እና 12.15 ሚሊየን ተመድቦለት ብር 21.38፤ 7.62 እና 7.09 ሚሊየን በበጀት ዓመታቱ ሥራ ላይ አውሏል፡፡ የካፒታል በጀትን በተመለከተ በነዚሁ ሦስት ተከታታይ የበጀት ዓመታት በቅደም ተከተሉ መሠረት ብር 15.62፤ 10.14 እና 8.72 ሚሊየን ተመድቦለት የነበረ ሲሆን፣ ብር 12.97፤ 30.91 እና 7.72 ሚሊየን ተጠቅሟል፡፡ በ2000 በጀት ዓመት ወጪው ከተፈቀደው በጀት በ20 ሚሊዮን በልጦ ሊታይ የቻለው ከውጪ ለገቡ እቃዎች በጉሙሩክ የተቀነሰው ሂሳብ በበጀት ሳይያዝ በወጪ ብቻ ተይዞ በባለሥልጣኑ የሂሳብ መግለጫዎቸ ላይ በመቅረቡ መሆኑን ከቀረቡ መረጃዎች ተረጋግጧል፡፡

## የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ

11. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ባለሥልጣኑ ከተቋቋመበት ዓላማ አንፃር የቅርስ ጥናት፤ ጥበቃና እንክብካቤ በአግባቡ መከናወኑን ለማረጋገጥና በቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ካሉ ችግሮቹን ለይቶ በማውጣት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለሥራ አመራሩ ለማቅረብ ነው።

## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

12. ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ1999  ስከ የ2001 በጀት ዓመታት በባለስልጣኑ የተከናወኑ ተግባራትን ነው፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ሲሆን፣ ከባለሥልጣኑ በተጨማሪ በሶስት ክልሎች ማለትም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የምዕራብ ጎጃም እና የሰሜን ጎንደር ዞኖች፣ በኦሮሚያ የባሌ ዞን እና በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰብ ሕዝቦች ክልል በጌዲዮ እና በጉራጌ ዞኖች በአካል በመገኘት በቅርስ ዙሪያ የተከናወኑ እና በመከናወን ላይ ያሉ ተግባራትን አስመልክቶ መረጃዎችን የመሰብሰብ እና ቅርሶች ያሉበትን ሁኔታ የማየት እና ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ የማቅረብ ተግባር ተከናውኗል፡፡ በአካል ላልተሄደባቸው ዘጠኝ ክልሎች መጠይቅ ተዘጋጅቶ በመላክ መልስ ከተሰጠባቸው ሁለት ክልሎች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## የኦዲቱ አካባቢ (AUDIT AREA)

13. ከላይ የተመለከተውን የኦዲት ዓላማ ለማሳካት ለዝርዝር የኦዲት ጥናቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ "ባለስልጣኑ በሀገሪቱ ቅርስ ላይ ተገቢውን የቅርስ ምዝገባ፣ ጥበቃና እና እንክብካቤ ለማከናወን የሚያስችለውን የአሠራር ስልት የዘረጋና በብቃትና በቁጠባ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (AUDIT ISSUES)

14. ለዝርዝር ኦዲቱ በተለየው የኦዲት አካባቢ ስር ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡ እነሱም:-

    1 በባለሥልጣኑ የሚከናወነው የቅርስ ምዝገባ፣ ጥበቃ እና እንክብካቤ በብቃትና በቁጠባ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም እና

    2 የቅርስ ጥናትና ጥበቃን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱንና በብቃት ተግባራዊ መሆኑን መገምገም

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

15. ለዝርዝር ኦዲቱ ለተመረጡት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (AUDIT ISSUES) 26 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) የተዘጋጁ ሲሆን፣ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት መረጃዎች የባለስልጣኑ ማkkሚያ አዋጅ፣ የተለያዩ መመሪያዎች፤ የባለሥልጣኑ የድርጊት መርሐ ግብር፣ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፤ የ5 ዓመታት ስትራቴጂክ ዕቅድ፤ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት፤ በUNESCO የተዘጋጁ እና ከተለያዩ ድረ-ገፆች (web sites) የተገኙ መረጃዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ ሥራው የሚመለከታቸው የባለሥልጣኑ የሥራ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ተደርጎ ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን፣ የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

## የቅርስ ጥናትና ጥበቃ የሥራ ሂደት መግለጫ (PROCESS DISCRIPTION)

16. ባለሥልጣኑ በመጀመሪያ ከተገልጋዮች በሚቀርበው ጥያቄ መሠረት በቅርስነት ሊያዙ የሚገቡ ጥናት እና ምርምር የሚያስፈልጋቸው ቁሶች መረጃን የማሰባሰብ ሥራ የሚያከናወን ሲሆን፣ በቀጣይ ቅርሱ በሚገኝበት ቦታ በመገኘት እና ጥናትና ምርምር በማድረግ ተጨማሪ መረጃ የማሰባሰብ፤ የመተንተን፤ የማጠናቀርና የጥናት ሰነድ ማዘጋጀት ተግባር ካከናወነ በኃላ  የማይዳሰስ ወይም ተንቀሳቃሽ ከሆነ ቅርሱን የማሰባሰብ ቋሚ ከሆነ ባለበት ቦታ መዝግቦ የመጠበቅ ተግባር ያከናወናል ፡፡

17. እነዚህን በተለያየ መንገድ የተሰበሰቡ ቅርሶች መቀበልና በደራሽ መዝገብ ላይ መመዝገብ፤ የላቦራቶሪ አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን ወደ ላቦራቶሪ የመላክ፤ ለቅርሶቹ መለያ ቁጥር መስጠት፣ ስለቅርሶቹ ሁኔታ መግለጫ ማዘጋጀት፤ በየደረጃቸው በመያዝ ማውጫ (catalogue) የማዘጋጀት ተግባር በማከናወን የቅርሶች መረጃ ወደ መረጃ ቋት ከተላከ በኋላ የተደራጁት ቅርሶች ለኢግዚቢሽን ይዘጋጃሉ፡፡

18. በቀጣይም ቅርሱን በማዕከል ማሰባሰብ ከተቻለ እና ከተሰበሰበ በማዕከል ጥበቃ እና እንክብካቤ የሚደረግለት፣ ይህን ማድረግ የማይቻል ከሆነ ግን ቅርሱ ባለበት ቦታ ጥበቃ እና እንክብካቤ የማድረግ ተግባር የሚከናወን ሲሆን፣ አግባብነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ቅርሶቹን በባለቤትነት በያዘው አካል እንዲጠበቁ ይደረጋል፡፡ የተመዘገቡ ቅርሶች በአግባቡ ጥበቃ እና እንክብካቤ እየተደረገላቸው መሆኑን በተመለከተ ክትትል በማድረግ እና በማረጋገጥ ሪፖርት ይቀርባል፡፡

19. ከጥናትና ምርምር፤ ከቅርስ ማሰባሰብ፤ ከጥበቃና እንክብካቤ እና ከተመራማሪዎች የላቦራቶሪ አገልግሎት ጥያቄ ሲቀርብ የቅርስ ላቦራቶሪ አገልግሎት የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ የካስት (cast) ሥራ እና የሥልጠና ጥያቄዎችንም በመቀበል በላቦራቶሪ ውስጥ ቅርሶችን የመመርመር፣ የመፈተሽና የማከም ሥልጠና አገልግሎት ይሰጣል፡፡ በላቦራቶሪ የተፈተሹ ቅርሶች ተጨማሪ ጥገናና እንክብካቤ ካስፈለጋቸው ጥገናና እንክብካቤ ወደሚያደርገው የሥራ ክፍል የሚላኩ ሲሆን፣ በላቦራቶሪ የተፈተሹ ቅርሶች ተጨማሪ ጥገናና እንክብካቤ የማያስፈልጋቸው ከሆነ ወደ ቅርሶች ማደራጃ ይላካሉ፡፡

20. በመጨረሻም የቅርስ መረጃዎች በፈርጅ በፈርጃቸው ተለይተው በመረጃ ቋትና በቅርስ ቤተ-መፃህፍት ውስጥ የሚደራጁ ሲሆን፣ መረጃዎቹን ለሥራ ሂደቱ ዋና ዋና ተግባራትና ለውጭ ተገልጋዮች የማሰራጨት፣ መጠባበቂያ (back up) መያዝ እና በመረጃ መረብ፣ በህትመት፣ በሚለጠፉ ማስታወቂያ ጽሁፎች (postrers)፣ በመፅሄት እና በሌሎች አመቺ መንገዶች የማሰራጨት ተግባር ይከናወናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ግኝቶች

## I. የቅርስ ምዝገባን በተመለከተ

### የቅርሶች ምዝገባ የሚሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ መመሪያ መዘጋጀቱን በተመለከተ

21. ቅርሶች እንዲጠበቁ ባለሥልጣኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የአመዘጋገብ መመሪያ ሊኖረው ይገባል፡፡

22. ባለሥልጣኑ የማይዳሰሱ (intangible) ቅርሶች መመዝገቢያ መመሪያ ያዘጋጀ ቢሆንም ለተንቀሳቃሽ እና ለቋሚ ቅርሶች በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የቅርስ ምዝገባ ለማከናወን የሚያስችል መመሪያ አላወጣም፡፡ ይህንንም በተመለከተ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ካገኘነው መረጃ እና የቢሮው የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣ መመሪያ ስላልደረሳቸው ለቅርስ ምዝገባ የሚጠቀሙባቸው መመሪዎች በቢሮ ደረጃ የተዘጋጁ መሆናቸውን፣ በዚህም ምክንያት በክልሉ እስካሁን የተከናወነው የቅርስ ምዝገባ ተገቢውን የቅርስ አመዘጋገብ መስፈርት የጠበቀ ነው ለማለት እንደማይቻል ገልጸዋል፡፡

23. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ካገኘነው መረጃ እና የቢሮው የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ለሁሉም አይነት ቅርሶች ምዝገባ የተዘጋጁ መመሪያዎች ከባለስልጣኑ የደረሳቸው መሆኑን እና ለቋሚ ቅርሶች የተዘጋጀውን መመሪያ እንደ ክልሉ ሁኔታ በማሻሻል የምዝገባ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ደረሰን ያሉዋቸው መመሪያዎች ሲታዩ መመሪያ ሳይሆኑ ቅፆች ብቻ መሆናቸውን አረጋግጠናል፡፡ በዚሁ ክልል ከጌዲኦ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው በዞኑ የሚገኙ ተንቀሳቃሽ፣ kሚ እና የማይዳሰሱ (intangible) ቅርሶች የተመዘገቡት በቅርስ አመዘጋገብ መመሪያ መሠረት አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

24. ይህንንም በተመለከተ የባለሥልጣኑ የቅርስ ኢንቬንቶሪ፣ ቁጥጥርና ደረጃ ማውጣት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ባለስልጣኑ የቅርስ ምዝገባ መመሪያ (manual) ሲያዘጋጅ ክልሎችን ባሳተፈ መልኩ ቢሆንም አሁን ተከሰተ የተባለው ችግር ከምን የተነሳ እንደሆነ እንደማያውቁ ገልጸዋል፡፡

25. በባለሥልጣኑ የተዘጋጁት የቅርስ መመዝገቢያ መመሪያዎች በአገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም ክልሎች እንዲደርሱ ባለመደረጉ እና ወጥ በሆነ መልኩ እየተሠራበት ባለመሆኑ የቅርስ አመዘጋገብ ሥራው ጥራቱን የጠበቀ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ ለቀጣይ የቅርስ አጠባበቅ፣ ጥገና እና እንክብካቤ ሥራ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

## ተንቀሳቃሽና ቋሚ ቅርሶች በቦታ ተለይተው ምዝገባ የተደረገላቸው መሆኑን በተመለከተ

26. ተንቀሳቃሽና ቋሚ ቅርሶች በሚገኙበት ቦታ በብዛት እና በአይነት ተለይተው ምዝገባ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

27. በባለሥልጣኑ በኩል ከ1972 ዓ.ም. እስከ 1985 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ወደ ሰባ ሺህ የሚጠጉ በተለያዩ ተቋማት እና በግለሰቦች እጅ የሚገኙ የማይንቀሳቀሱ እና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የተመዘገቡበት ሁኔታ ያለ ቢሆንም፤ በባለሥልጣኑ እና በክልሎች መካከል በቅርስ አመዘጋገብ የሥራ ሂደት ላይ ግልጽ የሆነ ኃላፊነት እንዲቀመጥ ባለመደረጉ እንዲሁም ቅርሱን በሚያስተዳድሩ አካላት እና ግለሰቦች የሚደረገው ትብብር አናሳ በመሆኑ ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ በባለሥልጣኑ አማካኝነት ተንቀሳቃሽ እና ቋሚ ቅርሶች ላይ ሊደረግ የሚገባው የምዝገባ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት በአግባቡ ያልተከናወኑ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

28. በናሙና ባየናቸው ሶስት ክልሎች ማለትም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ፤ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት–ጉራጌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት–ባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ከሰበሰብናቸው መረጃዎች ለመገንዘብ እንደተቻለው ደረጃውን የጠበቀ ምዝገባ ተከናውኗል ለማለት የማይቻል መሆኑን

ነው፡፡ በንጽጽር በkሚ ቅርሶች ላይ የተሻለ የመለየት እና የመመዝገብ ሥራ ቢከናወንም በተንቀሳቃሽ ቅርሶች ላይ የሚደረገው የምዝገባ ሥራ በመንገድ አለመኖር፣ በበጀት ማነስ እና በመሳሰሉት ምክንያቶች የመድረስ እና መረጃ የማግኘት ችግር በመፈጠሩ በእነዚህ ክልሎች የሚገኙት ቅርሶች ምዝገባ የተፈለገውን ያህል እንዳልተከናወነ፤ በተለይም በግለሰቦች እጅ ተይዘው የሚገኙ ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን የመመዝገብ ተግባር የሚጠበቀውን ያህል አለመሥራቱን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጌዲዮ ዞን ባህል እና ቱሪዝም ጽ/ቤት ለkሚ ቅርሶች የመለያ ቁጥር በመስጠት ምዝገባ ማከናወን ከዞኑ አቅም በላይ በመሆኑ የባለሥልጣኑ እገዛ አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

29. ከዚህም ሌላ በጎንደር ከተማ የሚገኝ የአዲስ ዓለም መስጊድ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተሠራ ቢሆንም ይህ ጥንታዊ መስጊድ በቅርስነት ያልተመዘገበ በመሆኑ በ1999 ዓ.ም. ፈርሶ በአዲስ መልክ የተሠራበትን ሁኔታ ቦታው ድረስ በመሄድ ከተገኘ መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡




*ምስል 1. በጎንደር ከተማ የሚገኘው ጥንታዊው አዲስ አለም መስጊድ ፈርሶ በአዲስ መልክ የተሰራ*

30. የባለሥልጣኑ የቅርስ ኢንቬንቶሪ፣ ቁጥጥርና ደረጃ ማውጣት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የቅርስ ምዝገባን አስመልክቶ በደሰሳ እና በቅኝት ኦዲት ወቅት

ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ በክልልና በፌደራል መንግስታት መካከል ቅርሶች መመዝገብን አስመልክቶ ግልፅ የሆነ የስራ ድርሻ ባለመኖሩ እና ባለሥልጣኑ በአጠቃላይ በቅርሶች ላይ በሚያደርገው የምዝገባ ሥራ ላይ ክፍተት መፈጠሩን እና ከግንዛቤ ማነስ የተነሳ በአንዳንድ አካባቢዎች ቅርሶችን አፍርሶ በዘመናዊ እና በአዲስ መልክ የመሥራት ሁኔታ እንደሚታይ የገለጹ ሲሆን፣ በተወሰነ ደረጃ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች በአብዛኛው በሰሜን ኢትዮÉያ በተለይም በአማራና በትግራይ፤ የኢንታንጀብል ቅርሶች ደግሞ በደቡብ ክልል የተመዘገቡበት ሁኔታ እንዳለ በዝርዝር ኦዲት ወቅት ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አያይዘውም በባለስልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 209/92 መሠረት በቅርስ አመዘጋገብ ዙሪያ ደንብና መመሪያ የማዘጋጀት ሥልጣን የባለሥልጣኑ በመሆኑ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ቢያቀርብም፣ የተዘጋጁ ደንቦችና መመሪያዎችን በሚመለከተው አካል አለመፅደቃቸውን ገልፀዋል፡፡

31. ቅርስን በሚመለከት የተዘጋጁ ደንቦችና መመሪያዎችን አለመጽደቃቸው እና በባለሥልጣኑ እና በክልሎች መካከል በቅርስ አመዘጋገብ የሥራ ሂደት ያላቸው የሥራ ድርሻ ግልጽ በሆነ መልኩ አለመቀመጥ የቅርስ ምዝገባ ሂደቱ በቀጣይነት ወጥ በሆነ መልኩ እንዳይከናወን ከማድረጉም በላይ ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች በብዛት እና በአይነት ተለይተው የሚገኙበት ሁኔታ እንዳይታወቅ አድር[1]ል፡፡

## የማይዳሰሱ ቅርሶች ምዝገባ በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተከናወነ መሆኑን በተመለከተ

32. ባህላዊና ታሪካዊ የማይዳሰሱ ቅርሶች በብዛት በአይነትና በስርጭት ተለይተው በሀገር አቀፍ ደረጃ መመዝገብ አለባቸው፡፡

33. ባለሥልጣኑ በተወሰኑ ክልሎች በማይዳሰሱ ቅርሶች ላይ ምዝገባ ያከናወነ ቢሆንም በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል ያልተመዘገቡበት ሁኔታ ታይቷል፡፡ በናሙና የተመረጡ የተለያዩ ባለ ድርሻ አካላት ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ቤተክርስቲያኒቷ ብዙ የማይዳሰሱ ቅርሶች ያሏት ቢሆንም እነዚህን ቅርሶች ለመጠበቅና ለመንከባከብ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት የሚደረግ እገዛ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡ የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቋሚ ቅርስ ጥገና ባለሙያ በሰጡን ምላሽ

የማይዳሰሱ ቅርሶች በክልሉ ጨርሶ ያልተመዘገቡበት ሁኔታ መኖሩን፤ የሰሜን ጎንደር ዞን ባህልን ቱሪዝም መምሪያ እና የባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች በማይዳሰሱ (intangible) ቅርሶች ላይ የሚደረገው የምዝገባ ሥራ አጥጋቢ አለመሆኑን፤ የአዲስ አበባ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በአሁኑ ሰዓት የቋሚ ቅርሶች ምዝገባ ብቻ የሚያከናውን መሆኑን፣ በማይዳሰሱ (intangible) ቅርሶች ላይ ግን ምዝገባ የማያከናወን መሆኑን ገልፀዋል፡፡

34. የባለሥልጣኑ የቅርስ ኢንቬንቶሪ፣ ቁጥጥር እና ደረጃ ማውጣት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በደቡብ ክልል ትኩረት የተሰጠው ቀደም ሲል ትኩረት ሳያገኝ የቆየ እና ብዙ ብሔረሰቦች የሚገኙበት አካባቢ በመሆኑ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

35. በባለስልጣኑ በማይዳሰሱ (intangable) ቅርሶች የምዝገባ ተግባራት ያከናወነው በአብዛኛው በደቡብ መሆኑን ለኦዲቱ ቀርበው ከታዩ የተለያዩ የቅርስ ምዝገባ መጽሄቶች እና የቅርስ ኢንቬንቶሪ፣ ቁጥጥርና ደረጃ ማውጣት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሰጡት ምላሽ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

36. የማይዳሰሱ (intangable) ቅርሶች ምዝገባ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲታይ በአብዛኛው በአንድ ክልል ላይ ማተኮሩ በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚገኙ የተለያዩ ብሔረሰቦች የማይዳሰሱ ባሕላዊ ቅርሶች ትኩረት አለመስጠቱ አዲሱ ትውልድ የራሱ የሆኑትን የማይዳሰሱ ቅርሶች እንዳያውቅ ያደርጋል፡፡

## የቅርስን ምዝገባ የሚያደርጉ ባለሙያዎች ሙያው የሚጠይቀው ክህሎት እና ሥነ ምግባር ያላቸው መሆኑን በተመለከተ

37. የቅርስን ምዝገባ የሚያደርጉ ባለሙያዎች ሙያው የሚጠይቀውን ክህሎት እና ሥነ ምግባር የሚያሟሉ ሊሆን ይገባል፡፡

38. በ1998 ዓ.ም. ባለሥልጣኑ ባዘጋጀው የ5 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ የሥነ ምግባር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ላይ ሶስት (የሙዚየም፤ የጥናትና ምርምር እና ምዝገባና ቁጥጥር) የሙያ ስነ ምግባሮችን አጥንቶ በሥራ ላይ ለማዋል በእቅድ ቢይዝም

በኦዲቱ በታዩት ከ1999-2002 ባሉ የሥራ ዘመናት ዓመታዊ ዕቅድ እና የዕቅድ ክንውን ሪፖርቶች ውስጥ ተካተው አልተገኘም፡፡

39. የቅርስ ምዝገባ የሚያከናውኑ ሠራተኞች የሙያ ብቃትን በተመለከተ የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የቅርስ ምዝገባ የሚያከናውኑ ባለሙያዎች የግዕዝ ቋንቋ ዕውቀት የሌላቸው ወይም ችሎታቸው በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በግዕዝ የተጻፉ ቅርሶችን ይዘት ለመረዳት የሚቸገሩበት ሁኔታ እንደሚታይ እና በቅርስ ምዝገባ ላይ ስህተት እንደሚፈጠር ገልጸዋል፡፡

40. የሥነምግባር ደንብ ለማዘጋጀት ዕቅድ ተይዞ ተግባራዊ አለመደረጉ እና የቅርስ ምዝገባ የሚያከናውኑ ባለሙያዎች ሙያው የሚጠይቀውን ስነምግባር በመከተል የሥራ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዳይወጡ ያደርጋል፡፡

41. የቅርስ ምዝገባ የሚያከናውኑ ባለሙያዎች ምዝገባ ስለሚደረግለት ቅርስ ይዘት በቀላሉ ለመረዳት ችሎታ ከሌላቸው ስለቅርሱ በቂ እና ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች ሳይመዘገቡ የሚቀሩበት ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በዚህም ምክንያት በቀጣይ ለቅርሱ ጥበቃ፣ ጥገና እና እንክብካቤ ለማድረግ አመቺ የሆነ ሁኔታ እንዳይፈጠር ያደርጋል፡፡

## ባለሥልጣኑ ለአርኪዮሎጂ ጥናት የሚውሉ ቦታዎችን ለይቶ ምዝገባ ማድረጉን በተመለከተ

42. ባለስልጣኑ ለአርኪዮሎጂ ጥናት የሚውሉ ቦታዎችን ለይቶ ምዝገባ ማድረግ አለበት፡፡

43. የአርኪዮሎጂ ጥናት ሊከናወንባቸው የሚችሉ ቦታዎች ለምሳሌ ትክል ድንጋዮች የሚገኙባቸውን ቦታዎች የመለየትና የመመዝገብ ሥራ በተወሰነ ደረጃ የተከናወነ ቢሆንም የአርኪዮሎጂ ጥናት እየተከናወነ የሚገኝባቸው ሆኑ ሊከናወንባቸው የሚችሉ ቦታዎች ሙሉ ለሙሉ ተጠንተው እና ተጠናቀው አለመመዝገባቸውን የጉራጌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ፅ/ቤት የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ገልፀዋል፡፡

የባለስልጣኑ የቅርስ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ደይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አክሱም፤ ላሊበላ፤ ጥያ፣ ወዘተ... የመሳሰሉት አስፈላጊ የሆኑ የአርኪዮሎጂ ጥናት የሚካሄድባቸው ቦታዎች የተመዘገቡ መሆኑን ሆኖም ሜዳማ የሆኑና አስፈላጊው የአርኪዮሎጂ መረጃ ተሰብስቦ የተጠናቀቀባቸው ቦታዎች ግን እንደማይመዘገቡ ገልፀዋል፡፡


44. ለአርኪዮሎጂ ጥናት የሚውሉ ቦታዎችን ተለይተው ካልተመዘገቡ በሀገሪቷ የአርኪዮሎጂ ጥናት ለማድረግ የሚመጡ ባለሙያዎችን በአግባቡ ለማስተናገድ እና ጥናት ሊከናወንባቸው በሚገቡ ቦታዎች ላይ ሙሉ በሙሉ ጥናቱ እንዲከናወን ለማድረግ አያስችልም፡፡

# II.የቅርስ ጥገናና እንክብካቤን በተመለከተ

## የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ተግባር መስፈርቱን በጠበቀ መልኩ የሚከናወን መሆኑን በተመለከተ

45. የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ሥራ ራሱን የቻለ መስፈርት (standerd) ሊኖረው እና ምዝገባውም መስፈርቱን በጠበቀ መልኩ መከናወን ይገባዋል፡፡

46. በባለሥልጣኑ የቅርስ ጥገና እና እንክብካቤ መስፈርት ያለው ቢሆንም፤ የኦዲት ቡድኑ ተዘዋውሮ ከተመለከታቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አንዳንዶቹ ለመጥቀስ ጎንደር ደብረብርሃን ስላሴ በመስፈርቱ መሠረት ቅርስነቱን ጠብቆ በኖራ መታደስ ሲገባው በሲሚንቶና በጭቃ ተጠግኖ ተግኝቷል፡፡ በአማራ ክልል የሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ቅርስ የሆኑ አብያተ ክርስቲያናትን ለማሳደስ ከመንግሥት አካላት በመስፈርቱ መሠረት በኖራ ካልሆነ እንዳያሳድሱ የሚከለከሉበት ሁኔታ መኖሩን ሆኖም እነዚህን ውድ ቅርሶች ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ለማደስ አስፈላጊ በሆነው የኖራ አቅርቦት ላይ በተፈጠረ ከፍተኛ ችግር ምክንያት በኖራ ማደስ እንዳልተቻለ እና መስፈርቱን ባልጠበቀ ሁኔታ እንዲታደሱ መንገድ መክፈቱን ገልጸዋል፡፡




*ምስል 2. በጎንደር የደብረ ብርሃን ስላሴ ቤ/ክርስቲያን በጭቃና በሲሚንቶ የተጠገነ*

47. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህልና ቱሪዝም ቢሮና ፓርኮች አስተዳደር ምክትል ቢሮ ኃላፊ ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በክልሉ ለሚገኙ በዓለም አቀፍ ቅርስነት የተመዘገቡ ቅርሶችን ለመጠገን ዋነኛ ግብዓት የሆነው ኖራ የሚመጣበት ቦታ መራቁ እነዚህ ቅርሶችን በወቅቱ እና በአግባቡ በመጠገኑ ረገድ ችግር እያስከተለ መሆኑን፤ ይህን ሁኔታ ለማቃለል ቅርሶቹ በሚገኙበት አካባቢ ኖራ ለማግኘት ጥረት እየተደረገ እንዳለ ገልፀዋል፡፡

48. የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የቅርስ ጥገና ራሱን የቻለ መርህ ቢኖረውም በአንዳንድ ቦታዎች ተደብቀው ደረጃውን ባልጠበቀ ሁኔታ ለቅርሶች አደሳ የሚያከናውኑበት ሁኔታ እንዳለና ይህንንም ድርጊት የሚፈፅሙት በአብዛኛው ከግንዛቤ እጥረት ሳይሆን ለቅርሶቹ የሚያስፈልገው የጥገና ወጭ ከፍተኛ በመሆኑ እና በባለሥልጣኑም በቅርስ ጥገና ዙሪያ የባለሙያ እጥረት በመኖሩ ጊዜያዊ ቅርስን የማቆየት ሥራ ለመሥራት ጥረት የሚደረግ ቢሆንም አፋጣኝ የጥገና ሥራ ለማከናወን ለሚጠይቁት ትብብር ወቅታዊ ምላሽ መስጠት ባለመቻሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

49. ባለስልጣኑ ባለበት የባለሙያ እጥረት እና የአቅም ውስንነት ምክንያት ቅርሶቹን በሚያስተዳድሩ አካላት ለሚቀርብለት ጥያቄ ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት አለመቻሉ በአንዳንድ ቦታዎች የቅርሶች ጥገና ጥንታዊ ይዘቱን ሳይጠብቅ የሚከናወንበትን

ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ይህም ሊገኙ የማይችሉ ጥንታዊ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመዘገቡ የሀገሪቱ ቅርሶችን ለጉዳትና ለብልሽት ሊዳርግ እና በሂደትም እንዲጠፉ ለማድረግ የጎላ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

## ለቅርስ ጥገና እና እንክብካቤ ዙሪያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ የሚሰጥ መሆኑን በተመለከተ

50. የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን በቅርስ ጥገና እና እንክብካቤ ዙሪያ በተገልጋዮች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡

51. ባለሥልጣኑ በቅርሶች ጥበቃ፣ እንክብካቤና ጥገና ዙሪያ በተገልጋዮች ለሚቀርቡ የድጋፍ ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ እየሰጣቸው አይገኝም፡፡ በዚህም ምክንያት በዓለም አቀፍ ቅርስነት የተመዘገቡ እና በጎንደር ከተማ እና ዙሪያ የሚገኙ ቋሚ ቅርሶች (አብያተ ክርስቲያናት፣ ገዳማት፣ ቤተ መንግስታት) ጉዳት እየደረሰባቸው መሆኑን በአካል ቦታው ላይ በመመልከት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የጎንደር ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ከላይ የተቀመጠው ሁኔታ ትክክል መሆኑን በመግለጽ በጎንደር ከተማ የሚገኘው የደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተክርስቲያን በሲሚንቶ እና በአፈር መጠገንን እንደምሳሌ ጠቅሰዋል፡፡

52. በተጨማሪም በጣና ደሴቶች ላይ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ማለትም በመሀል ዘጌ ጥንታዊው የአቡነ በትረ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጥገና ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ በበጀት ማነስ መቋረጡ ከቤተ ክርስቲያኑ ገበዝ የተገለጸ ሲሆን፤ ዑራ ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን ላይ መጠነኛ ጉዳት እንደደረሰ እና ወቅታዊ ጥገና እንዳልተደረገለት በአካል በቦታው ላይ በመገኘት ለመመልከት ተችሏል፡፡ ከሰሜን ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ከተገኘው መረጃ ለመገንዘብ እንደተቻለው በዞኑ በሚገኙ ጥንታዊ አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት ውስጥ በአግባቡ ያልተያዙ በርካታ ጥንታዊ እና ውድ ቅርሶች ያሉ መሆኑን፤ ለመጥቀስ ያህል በደረስጌ ቅድስት ማርያም፤ ሰረባር ባዓለ እግዚአብሄር፤ ደቋ ኪዳነ ምህረት፤ ወዘተ... አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም በጣና ሐይቅ ሰሜናዊ ጫፍ ጎርጎራ አካባቢ የሚገኙ የደንቀዝ የአፄ ሱስንዮስ ቤተ መንግስት እና የካቶሊክ ካቴድራል ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ እንደልተደረገላቸው እና በአሁኑ ወቅት በመፈራረስ እና በመጥፋት ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡



ምስል 3፡ ተገቢው ጥበቃ አና እንክብካቤ ያልተደረገላቸው በሰሜን ጎንደር ዞን በደንቀዝ የአፄ ሱስንዮስ ቤተ መንግስት እና የካቶሊክ ካቴድራል



*ምስል 4፡ በአግባቡ ያልተያዙ በሰሜን ጎንደር ዞን ጥንታዊ ውድ ቅርሶችን የያዘችው ደረስጌ ማርያም*

53. በጎንደር ከተማ የሚገኘው የእቴጌ ምንትዋብ ቤተ መንግሥት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ፈርሶና ሳር በቅሎበት፤ በዚሁ ግቢ በቁስቋም ማርያም ሙዝየም የጣሪያው እንጨት በፍሳሽ ውኃ ተበላሽቶና ሳር በቅሎበት እንደሚገኝ በቦታው ተገኝቶ ለማየት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የትግራይ ክልል ባህልና ቱሪዝም ኤጀንሲ ከባለስልጣኑ እንዲደረግላቸው ከሚፈልጉት የተለያዩ የአቅም ማጎልበቻ ድጋፍ በተጨማሪ በክልሉ በመጎዳት ላይ ለሚገኙ ቅርሶች እየደረሰባቸው ካለው ጉዳት በቅርበት እና በወቅቱ ለመጠበቅ በራሳቸው ጥገና ማካሄድ እንዲችሉ የጥገና ፈቃድ እንዲሰጣቸው ፍላጎት እንዳላቸው

ገልፀዋል፡፡ ይህንንም በተመለከተ ቢሆንም የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በባለስልጣኑና በክልሎች መካከል በቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ዙሪያ ያላቸው ኃላፊነት በተመለከተ በተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ ላይ ለቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ፍቃድ የመስጠት ኃላፊነት የባለስልጣኑ መሆኑን፣ አቅም ላላቸው ክልሎች በተወሰነ መልኩ ጥገና እንዲያደርጉ ፍቃድ የተሰጣቸው በመሆኑ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ኤጀንሲ የተሰጠው አስተያየት አግባብ እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡

54. በቅርስ ጥገና ዙሪያ ለሚቀርቡ የፈቃድ እና የትብብር ጥያቄዎች ወቅታዊ የቅርስ ጥገና ምላሽ መስጠት አለመቻሉ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመዝግበው የሚገኙ ቅርሶች ለአደጋ ከማጋለጡም በላይ እስከ መጨረሻው ሊታጡ የሚችሉበትን ሁኔታን ያስከትላል፡፡

## ለቅርስ ጥገና እና እንክብካቤ ሥራ የሚረዱ የተለያዩ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች መዘጋጀትን በተመለከተ

55. የቅርሰ ላቦራቶሪ አጠቃቀም እና በዓለም አቀፍና በአገር ውስጥ ባሉ ሙዚየሞች መካከል የሚደረግ የቅርስ ውሰት መመሪያ እንዲሁም የቅርስ ማስወገድና ማሰባሰብ ፖሊሲዎች ሊዘጋጁ እና ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

56. በባለሥልጣኑ ተጠንቶ ከየካቲት 2002 ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ባለው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት (BPR) ላይ የቅርስ የላቦራቶሪ አጠቃቀም መመሪያ እና የቅርስ ማስወገድ ፖሊሲ እንደሚያስፈልጉ የተጠቀሰ ቢሆንም እነዚህ ለቅርስ ጥበቃ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎች እና ፖሊሲ በኦዲት ወቅት ተጠይቀው ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡ በሙዝየሞች መካከል ለሚደረግ የቅርስ ውሰት መመሪያ በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀ ቢሆንም ጸድቆ ሥራ ላይ እንዲውል አልተደረገም፡፡

 የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ይህን በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ እነዚህን ሰነዶች እና መመሪያዎች በባለስልጣኑ በኩል ተዘጋጅተው ለባህል እና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቀረቡ ቢሆንም በሚኒስቴሩ በኩል እስካሁን ምላሽ እንዳልተሰጠ እና እንዳልፀደቁ ገልፀዋል፡፡

57. የላብራቶሪ አጠቃቀም መመሪያ አለመኖር በላቦራቶሪ ውስጥ መከናወን ያለባቸው ተግባራት ማለትም የተጠቃሚዎች ሥርዓት እና ደንብ እና የላብራቶሪ ተጠቃሚዎች ክፍያ በአግባቡ ህግ እና ደንብን ተከትለው እንዳይከናወኑ ያደርጋል፡፡ በዓለም አቀፍም ሆነ በሀገር ውስጥ ባሉ ሙዚየሞች መካከል ለሚደረጉ የቅርሶች ውሰት መመሪያ ጸድቆ ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ በእነዚህ ሙዝየሞች መካከል የሚደረጉ የቅርስ ዝውውር ተግባራት አስፈላጊውን ደረጃ ጠብቆ እንዳይከናወን፣ በቅርሶች ውሰት እና አመላለስ ወቅት ቅርሶችን ለጉዳት እና ለስርቆት እንዲጋለጡ፣ ከዚህም በተጨማሪ የሙዚየም ባለሙያዎች ብልሹ አሠራር እና ተጠያቂነት ያልሰፈነበት ተግባር እንዲያከናውኑ በር ይከፍታል፡፡ የቅርስ ማሰባሰብ ፖሊሲ አለመኖር ደግሞ በሥራ ሂደቱ የሚሰበሰቡ ቅርሶችን መጠን እና አይነት መለየት እና የቅርስ እሴታቸውን ሊያጡ የሚችሉ ቅርሶች ላይ በአግባቡ እና በወቅቱ እርምጃ እንዳይወሰድ ያደርጋል፡፡

## ከባለሥልጣኑ እውቅናና ፈቃድ ውጪ ቅርሶች ላይ ጥገናና እንክብካቤ ሲደረግ ህጋዊ እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ

58. ከባለስልጣን መ/ቤቱ ዕውቅና እና ፈቃድ ውጭ በቅርሶች ላይ ጥገናና እንክብካቤ እንዳይደረግ ተገቢው ቁጥጥር እና ክትትል መደረግ አለበት፡፡


59. በአንዳንድ ክልሎች ከባለስልጣን መ/ቤቱ ፍቃድ ሳያገኙ በቅርሶች ላይ ጥገና የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩን በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች ከተሰበሰበ መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የአማራ፤ የኦሮሚያ እና የደቡብ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች በክልላቸው ከተመዘገቡ ቅርሶች መካከል በአቅማቸው ጥገና ለማድረግ ሲታሰብ በቅድሚያ ለባለስልጣኑ በማሳወቅ እና በመነጋገር በጋራ እንደሚጠግኑ ቢገለፁም በዓለም አቀፍ ቅርስነት የተመዘገበው የጎንደር ደብረ ብርሐን ሥላሴ ላይ ከባለሥልጣኑ ፍቃድ ሳይገኝ በጭቃና በሲሚንቶ ጥገና ተደርጎ ተገኝቷል፡፡ ይህን ባደረጉ አካላት ላይ ክትትል በማድረግ ይህ ጎጂ ተግባር እንዳይበረታታ ተገቢ የማስተማሪያ እርምጃ አለመወሰዱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአዲስ አበባ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳይጠየቅ ጥንታዊ የሆነውን የደጃዝማች አያሌው ብሩ ቤትን ለመጠገን ከሕንፃ ተቋራጭ (contractor) ጋር ውል የፈፀሙበት ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

60. የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ብዙ ጊዜ በቅርሶች ላይ ያለ ባለሥልጣኑ ፈቃድ የሚደረጉ ጥገናዎች እንዳሉ የሚታወቅ መሆኑን፤ ይህን በቅርሶች ላይ እየተከናወነ ያለ ሕገወጥ  እና ደረጃውን ያልጠበቀ ጥገና ለመከላከል የክልሎችና የሚመለከታቸው  ባለድርሻ አካላት ትብብርን እንደሚጠይቅ ገልጸዋል፡፡

61. ከባለስልጣኑ መ/ቤቱ ፈቃድ ውጭ የሚደረግ የቅርስ ጥገና አስፈላጊ የሆኑ የጥገና መስፈርቶችን ላያሟላ ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በህገወጥ መንገድ የሚደረግ ጥገና የቅርሱን ማንነትና እሴት የሚያጠፋ እና የነበረውን ውበት የሚቀንስ ይሆናል፡፡

62. በባለስልጣን መ/ቤቱ እውቅና እና ፈቃድ ተሰጥቶ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ ሲደረግላቸው ጥገና እንክብካቤው በተቀመጠው የጥገና ደረጃ (standard) መሠረት ለመከናወኑ ባለሥልጣኑ ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ አለበት፡፡

63. በናሙና ተመርጠው ከታዩ ቦታዎች መካከል በአማራ ክልል በጎንደር ከተማ የአፄ ፋሲል ቤተመንግስት ከስምንት አመታት በፊት ጥገና የተደረገለት ቢሆንም ተጠገነ የተባለው ህንፃ የመሰነጣጠቅ አደጋ እንደደረሰበት የኦዲት ቡድኑ በአካል በመመልከት አረጋግጧል፡፡ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ጉዳዩን እንደማያውቁትና ካለው የጥገና ቁሳቁስ እጥረት አንፃር የሚከናወኑ ጥገናዎች የቅርስ ጥገና መስፈርት ደረጃን በጠበቀ ሁኔታ ለማከናወን አስቸጋሪ እና ከባድ መሆኑን በጎንደር ከተማ ውስጥ የሚገኘው የዓለም አቀፍ ቅርስ (የአፄ ፋሲል ግቢ) ከስምንት አመት በፊት ከፍተኛ ጥገና ሲደረግለት ጉዳት የደረሰበትን በመምረጥ የማጠናከር ወይም የመተካት ስራ ቢከናወንም በተለያየ ጊዜ አዳዲስ ጉዳቶች ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ሊፈጠሩ መቻላቸውን፣ በዚህ ወቅትም ጉዳቱን በመለየት የማጠናከሪያ ሥራ መሠራቱን፣ አንዳንዶቹም በፍራሽነታቸው እንዳሉ ተጠብቀው ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ የመከላከል ሥራ እንደሚከናወን ገልጸዋል፡፡




**ምስል 5፡ በጎንደር ከተማ የሚገኘው ተጠገነ ተብሎ የመሰነጣጠቅ አደጋ የደረሰበት የአፄ ፋሲል ግንብ**

64. ቅርሶች በጥገና ወቅት አስፈላጊውን ደረጃ ጠብቀው መጠገናቸውን ክትትል አለመደረጉ የነበረ ይዞታቸውን ጠብቀው እንዳይቆዩ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ መቆየት ካለባቸው ጊዜ ቀድመው የመበላሸት አደጋ እንዲከሰት ያደርጋል፡፡

# III.የቅርስ አጠባበቅና አያያዝን በተመለከተ

## ለቅርስ አጠባበቅ ትኩረት መሰጠቱን በተመለከተ

65. የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ለቅርስ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት በቅርስ አጠባበቅ፣ ዙሪያ ለሚቀርብለት ጥያቄ ወቅታዊ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡

66. ለቅርስ ጥበቃ ተገቢው ትኩረት ባለመሰጠቱ እና በቅርስ አጠባበቅ ዙሪያ ለሚቀርብ የድጋፍ ጥያቄ ወቅታዊ ምላሽ ባለማግኘቱ ብዛት ያላቸው ቅርሶች ለጥፋት የተጋለጡበት ሁኔታ ታይቷል፡፡ የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ በሀገረ ስብከቱ ለቱሪስት መስህብነት ሊውሉ የሚችሉ ብዙ ውድ ቅርሶችን የያዙ ገዳማት ቅርሱን ለመጠበቅ ታማኝ የሆኑ ጠባቂዎች ለመቅጠር በቂ በጀት ስለሌላቸው ታማኝ ናቸው ተብለው በኅብረተሰቡ በሚታመኑ ግለሰቦች ቤት እንዲጠበቁ እየተደረገ እንደሆነ፤ ሆኖም እነዚህ ግለሰቦች ቅርሶቹን በመጠበቃቸው የሚያገኙት ጥቅም ስለሌለ ተረከቡን የሚል ጥያቄ በተደጋጋሚ እንደሚያቀርቡ፤ የሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ቅርሶች የሚጠበቁት በአካባቢው ተወላጅ የሆኑና ታማኝ ናቸው ተብለው በሚታጩ ግለሰቦች ሲሆኑ፣ እነዚህ ሰዎች በቅርስ ዙሪያ ተገቢው ልምድ አላቸው ለማለት የማያስችል ከመሆኑም በላይ ቅርስን በግለሰቦች ቤት ማስቀመጡ ለጊዜው ጠቀሜታ ያለው ቢመስልም በቀጣይ እነዚህ ግለሰቦች ቅርሱን ሳያስረክቡ በድንገት ከዚህ ዓለም ሲያልፉ እና ትውልድ እየተተካ ሲሄድ ከባለቤትነት ጋር በተያያዘ ችግር እያስከተለ እንደሆነ እና ወደፊትም ሊያስከትል እንደሚችል አስረድተዋል፡፡

67. በአማራ ክልል በናሙና ባየናቸው ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፤

- በምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት፤
  - በጣና ደሴት በሚገኘው የክብራን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ሙዝየም ጠባቂና አስጎብኝ አባት በገዳሙ የሚገኙትን ቅርሶች አጠባበቅ በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡን መልስ ለረጂም ዘመናት የቆዩ የነገስታት ጠፍር አልጋዎች፣ ደውል፣ ነጋሪት ወዘተ… በገዳሙ ሙዝየም ውስጥ መቀመጥ የሚገባቸው

ቢሆንም ሙዝየሙ ጠባብ በመሆኑ በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ እንዲቀመጡ የተደረጉበት ሁኔታ መኖሩን፤

- በጣና ደሴት በምትገኘው የዑራ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ሙዝየም ኃላፊ በቤተ ክርስቲያኗ የሚገኙ ቅርሶች አጠባበቅን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ በበጎ አድራጊ ምዕመናን የተሠራ የመስተዋት ቁም ሳጥን በመኖሩ የተወሰኑት ቅርሶች እንዲቀመጡበት የተደረገ ቢሆንም በገዳሙ ካሉት ቅርሶች ብዛት አንፃር በቂ እንዳልሆነ፤ በሙዝየሙ ጠባብነት የተነሳ ከ1297-1327 በንጉሥ ዓምደ ፅዮን ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የነበረ የቤተክርስቲያን ጉልላት መቀመጫ አጥቶ ውጭ እንዲቀመጥ መደረጉን፤
- በጣና ደሴት በሚገኘው በአቡነ በትረ ማርያም ቤተክርስቲያን ቁልፍ ያዥና አስጎብኚ በቤተ ክርስቲያኗ የሚገኙ ቅርሶች አጠባበቅን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተቀመጡ ቅርሶች በቤተ ክርስቲያኑ ሙዝየም ውስጥ የሚገኙ እና በአገልግሎት ብዛት የተጎዱ የብራና የጥንት መፅሀፍት በከፊል ያሉ ቢሆንም ጥገና እንዳልተደረገላቸው፤ በቅርቡ የሙዝየሙ ጣሪያ ወደ ቆርቆሮ ክዳን የተቀየረ ቢሆንም ሽኮኮ የምትባል አውሬ በሌሊት በጣሪያው እየገባች የሙዝየሙን ግድግዳ በመፈርፈር ቅርሱን የማበላሸት ሁኔታ እንደሚታይ፤ በ2002 ዓ.ም የካቲት 5 ቀን ጥንታዊው የመሀል ዘጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ባልታወቀ ምክንያት ሙሉ በሙሉ በመቃጠሉ ውድ የሆኑ ጥንታዊ ቅርሶች ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር አብረው መቃጠላቸው፤

- በሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት በጎንደር ከተማ የሚገኘው የደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ በቤተ ክርስቲያኑ የሚገኙ ቅርሶች አጠባበቅን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ በቤተ ክርስቲያኒቱ የቅርስ ማስቀመጫ የሚሆን ሙዝየም ባለመኖሩ በቅርሶች አቀማመጥ ላይ ችግር ያለ በመሆኑ ያሉት ቅርሶች ለደህንነታቸው አመቺ ባልሆነ ሁኔታ የተያዙ እንዲሁም ለአጠባበቅ በሚያመች ሁኔታ በሙዝየም ያልተቀመጡ በመሆኑ ጉብኝት የሚደረግበት ህንፃ ቤተክርስቲያኑ ብቻ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

68. የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ በሀገረ ስብከቱ ቅርስ ባለባቸው ገዳማት የሚገኙ ነባር እና ቀደምት አባቶች በእርጅና እየደከሙ የሚገኙበት ሁኔታ እየጎላ መምጣቱን፣ በየጊዜው የሚመጡ እና የሚለቁ ወጣኒ[1] መነኮሳት ወደ ገዳሙ ሲገቡና ሲወጡ ስለማንነታቸው የማጣራት እና የመከታተል ተግባር ከአቅም በላይ እና አስቸጋሪ እንደሆነ፣ ይህ ሁኔታም በገዳሙ የሚገኙ ቅርሶችን ከመጠበቅ አኳያ አደጋ እንደሚኖረው እና ትክክል እንዳልሆነ እንዲሁም ብዙዎች ውድ ቅርሶችን ይዘው እየጠበቁ ያሉ ገዳማት የሚተዳደሩበት ስለሌላቸው ብርቅዬ እና ውድ ቅርሶችን በያዙት በእነዚህ ገዳማት የሚገኙ መነኮሳት የሚበሉት በማጣት በከፍተኛ ችግር ላይ እንደሆኑና ገዳማቱን ለቀውም በመሄድ ቅርሶቹን የሚጠብቅ አካል እየጠፋ እንደሆነ፣ በእዚህም የተነሳ በቅርሶች ላይ ከፍተኛ ጥፋት እየደረሰ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

69. በምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት የአቡነ በትረማርያም ቤተ ክርስቲያን የቅርስ ሙዝየም ጠባቂ በእድሜ የገፉ (90 ዓመት የሆናቸው) በመሆኑ ሌላ ታማኝ ሰው ለመተካት በተደረገው ጥረት በአካባቢው ምዕመናን የተመረጡት ግለሰብ ቅርሱን እንዲረከቡ ቢጠሩም ባለመገኘታቸው እስካሁን ተተኪ ቅርስ ጠባቂ ለማስቀመጥ እንዳልተቻለ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ አስረድተዋል፡፡

እነዚህን ጉዳዮች በተመለከተ የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቋሚ ቅርስ ጥገና ባለሙያ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በክልሉ ውስጥ ብዛት ያለው ቅርስ ቢኖርም ወቅታዊነትን የጠበቀ ትኩረት ለቅርሶች ተሰጥቷል ማለት እንደማይቻል አስረድተዋል፡፡

[2] ወጣኒ ማለት ወደ ምንኩስና ህይወት ለመግባት በአመክሮ ወይም በመጠባበቅ ላይ ያለ ማለት ነው፡፡



*ምስል 6. በሌላ ጠባቂ እንዲተኩ ጥረት ቢደረግም መፍትሄ ያላገኙት ዕድሜአቸው 90 ዓመት በላይ የሆናቸው በጣና መሀል ዘጌ ደሴት የአቡነ በትረ ማርያም ቅርስ ጠባቂ*

70. የደቡብ ክልል የጉራጌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊዎች በዞኑ የሚገኙ ቅርሶች አያያዝን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ በሃይማኖት ተቋማት ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የመሰረቅ አደጋ በሰፊው እንደሚያጋጥማቸውና አቀማመጣቸው ለብልሽት በሚያጋልጣቸው ሁኔታ እንደሆነ፤ በቅርስ ዙሪያ ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ቅርሶቹን ለመመዝገብ እና ያሉበትን ሁኔታ ለመገምገም በሚሄዱበት ወቅት ቅርሶቹን ለማሳየት ተባባሪ አለመሆን፤ ቅርሶች ባሉባቸው የሃይማኖት ተቋማት ያለውና ቅርሱን ሊጠብቅ የሚችለው የተቋማቱ ማኅበረሰብ ቁጥር መመናመን ዋና ዋና ችግሮች መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

71. የደቡብ ክልል የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች በብዛት የሚገኙበት ክልል እንደመሆኑ መጠን የኅብረተሰቡን ባህል ለማሳየት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የሙዝየም አይነቶች ቢያስፈልጉም በበጀት እጥረት ምክንያት አጥጋቢ ሥራ እንዳልተሠራ በክልሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የብዝሀ ባህል አስተባባሪ የገለጹ ሲሆን፣ የጌዲኦ እና የጉራጌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ደግሞ ተንቀሳቃሽ ባህላዊ ቅርሶችን በመሰብሰብ በተወሰነ ደረጃ በአንድ ክፍል ውስጥ የማስቀመጥ ሥራ የተሠራ ቢሆንም ደረጃውን የጠበቀ ቅርሶችን ለመጠበቅ የሚያስችል ሙዝየም በዞናቸው የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

72. በሌላ በኩል የኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ምክትል ቢሮ ኃላፊ እና የባህል ዘርፍ ኃላፊ በክልሉ የሚገኙ ሙዝየሞች አደረጃጀት ደረጃን የጠበቀ ባይሆንም በኦሮሚያ ክልል ወደ 10 የሚጠጉ የቅርስ ሙዝየሞች እንደሚገኙ፤ ሆኖም በእነዚህ ሙዝየሞች ተመድበው የሚሠሩ ሠራተኞች ለሙያው ብቁ የሆኑ አለመሆናቸውን እና የሚጠበቀውን ያህል ሙዝየሞች በተሟላ ሁኔታ አለመኖራቸውን፤ አስረድተዋል፡፡

73. በባለስልጣኑ የቅርስ ኢንቬንቶሪ ቁጥጥርና ደረጃ ማውጣት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስለሁኔታ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ላሉ ችግሮች የዕምነት ተቋማት የራሳቸው አካሄድ ያላቸው በመሆኑም ቅርሶችን ለመጠበቅ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል የመቅጠር ተግባር ማከናወን የውስጥ ጉዳያቸው በመሆኑ እንደማይመለከታቸው ገልፀዋል፡፡

74. ቅርስን በግለሰቦች ቤት ማስቀመጡ ለጊዜው ጠቀሜታ ያለው ቢመስልም በቀጣይ እነዚህ ግለሰቦች ቅርሱን ሳያስረክቡ በድንገት ከዚህ ዓለም ሲያልፉ እና ትውልድ እየተተካ ሲሄድ ከባለቤትነት ጋር በተያያዘ ችግር እንደሚያስከትል፣ ቅርስን የያዙ አብያተ ክርስቲያናት ቅርሱን በመጠበቁ ረገድ ለሚታይባቸው የአቅም ውስንነት በቅርበት ሆኖ ድጋፍ ማድረግ ካልተቻለ ለዘመናት ሲጠብቋቸው የነበሩ ውድ ቅርሶች ዳግም ለማግኘት በማይቻልበት ሁኔታ ለጥፋት እና ለውድመት እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለቅርሶች በአግባቡ መቀመጥና መጠበቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ሙዝየም ደረጃውን በጠበቀ መልኩ አለመደራጀት ቅርሶችን ለጥፋትና ብልሽት ከመዳረጉም በላይ ጎብኝዎች ሲገቡም ሆነ ሲወጡ ፍተሻ ስለማይደረግ ቅርሶች ለስርቆት ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡

## የቅርስ አስተዳደር ሰነድ (Heritage Managment plan) መዘጋጀቱን በተመለከተ

75. ባለሥልጣኑ ለሚጠብቃቸው ቅርሶች የቅርስ አስተዳደር ሰነድ (heritages management plan) ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

76. በዓለም አቀፍ ቅርስነት ከተመዘገቡት ቅርሶች መካከል ለሰሜን ተራሮች ፓርክና ለሐረር ግንብ የቅርስ ቦታዎች አስተዳደር ሰነድ (heritage site management plan) የተዘጋጀላቸው ሲሆን፣ በዓለም አቀፍ ቅርስነት ለተመዘገበው (ፋሲል ግቢ)

የቅርስ አስተዳደር ሰነድ ቢዘጋጅም ያልፀደቀ መሆኑን፣ ለተቀሩት ዓለም አቀፍ የቅርስ ቦታዎች የአስተዳደር ሰነድ (site management plan) ያልተዘጋጀ መሆኑን ከአማራ ክልል ካገኘነው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

77. በደቡብ ክልል የጉራጌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊዎች በዞኑ በሚገኙ የቋሚ ቅርስ (ትክል ድንጋዮች የሚገኙባቸው) ቦታዎች መካከል በሁለት ላይ ብቻ ጉዳት እንዳይደርስባቸው በአጥር በመከለልና ጠባቂ በማስቀመጥ መጠነኛ ሥራ የተሠራ እና በአንዱ ላይ የአካባቢው ማኅበረሰብ እራሱ ጥበቃ እያካሄደ ቢሆንም የተወሰኑት ይዞታቸው በግለሰብ እጅ በመሆኑ ዙሪያቸውን የእርሻ ሥራ ስለሚከናወንባቸው፣ ሌሎቹ ደግሞ በርቀት በመገኘታቸው የመውደቅ እና የመሰረቅ አደጋ እያጋጠማቸው እና ከጥፋት የመከላከል ሥራ ለመሥራት እንዳልተቻለ ገልፀዋል፡፡





*ምስል 7. ቱቲፈላ ትክል ድንጋይ የመከላከያ ክልል ሳይኖረው ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅሎ ያለበት ሁኔታ*

78. የሰሜን ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ በጎንደር ከተማ የሚገኙ ቅርሶች ከህብረተሰቡ ጋር ተሰባጥረው የሚገኙ እና ከጥፋት ለመጠበቅ የሚያግዝ የመከላከያ ክልል (Buffer zone) የሌላቸው በመሆኑ የትኛውም ተሽከርካሪ በቅርብ ርቀት ስለሚንቀሳቀስ በቅርሱ ላይ አደጋ እየደረሰ መሆኑንና ይህንን በቅርሱ ላይ እየደረሰ ያለውን ጥፋት ለማቃለል ጥረት እየተደረገ ቢሆንም በቀጣይ ሰፊ ጥረትና በጀት እንደሚጠይቅ ገልፀዋል፡፡

79. በአፄ ፋሲል ቤተ መንግስት ላይ

- በፋሲል ግንብ ዙሪያ ቅርሱን ከጥፋት ለመጠበቅ የሚያግዝ  የመከላከያ ክልል (Buffer zone) ስለሌለ ተሽከርካሪዎች የሚንቀሳቀሱ በመሆኑ ለአደጋ መጋለጡን
- አንዳንድ ጎብኝዎች ግንቡን በመፈርፈር አላስፈላጊ ፅሁፍ የሚፅፉበት ሁኔታ መኖሩን፤
- በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በሚገኙ ቤተ ክርስቲያናት  የቀብር ስነስርዓት የሚካሄድበት መሆኑን፤
- የጎብኝዎች መብትና ግዴታ በማስታወቂያ ሰሌዳ ያልተዘጋጀ መሆኑን፤
- ቤተ መንግሥቱን የሚከልል ምንም አይነት ግንባታ መካሄድ የሌለበት ቢሆንም አካባቢው ትላልቅ ፎቆች የተሰሩበት ሁኔታ መታየቱን፤
- የጎንደር ማተሚያ ቤት በቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን፤

የኦዲት ቡድኑ በአካል በመጎብኘት ተመልክቷል፡፡

80. ከዚህም በተጨማሪ ይህ ቦታ የተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ማስፈፀሚያ ለምሳሌ የሠርግ ሥርዓት እና የቁንጅና ውድድር የሚካሄድበት፣ በርካታ ሰዎች በመስተናገዳቸው የፅዳት ችግር የሚፈጥር መሆኑና በቅርሱ ላይ ጉዳት የሚደርስበት ሁኔታ የጎላ እንደሆነ ከጎንደር ዓለም አቀፍ ቅርሶች አስተዳዳሪ ገለፃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት ስራ አስኪያጅ ከዓለም አቀፍ ቅርስ ስምምነት አንፃር ጎብኝም ሆነ አስጎብኝ ያላቸው መብትና ግዴታዎች በግልፅ አለመቀመጡን አስረድተዋል፡፡



*ምስል 8. በፋሲል ግንብ ዙሪያ ተሽከርካሪዎች የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ለአደጋ መጋለጡ*



ምስል 9. በጎብኝዎች ፅሁፍ የተፃፈበት የፋሲል ግንብ



ምስል10፡ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በሚገኙ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ የቀብር ሥነ ሥርዓት የሚካሄድበት፤



*ምስል 11. በጎንደር ከተማ የፋሲል ቤተ መንግሥትን ከሚከልሉ እና በቅርሱ ዙሪያ ከተሠሩ ትልልቅ ሕንፃዎች አንዱ*



ምስል 12. በጎንደር ከተማ የፋሲል ቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ የሚገኝ የጎንደር ማተሚያ ቤት

81. በዓለምአቀፍ ቅርስነት ለመያዝ እንደ አንድ ዋነኛ መስፈርት የሚታየው የቅርስ ቦታዎች አስተዳደር ሰነድ አለመኖር በሀገሪቷ በዓለም አቀፍ ቅርስነት ተመዝግበው የሚገኙ የአስተዳደር ሰነድ ያልተሠራላቸውን ቅርሶችን ከዓለም አቀፍ ቅርስነት ሊሰረዙ የሚችሉ ቅርሶች ዝርዝር (endangerd list) ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋቸዋል፡፡ በተጨማሪም ዕቅዱ ባለመኖሩ እስካሁን ድረስ ሊደረግ የነበረውን ጥገና፣ እንክብካቤ እና የቅርሶች ጥበቃ ወቅታዊ የሆኑ ችግሮች ላይ ያተኮረ የቅርስ ተገልጋዮችን ፍላጎት ያላሟላና ቀጣይነትና ተከታታይነት የሌለው እንዲሆን አድርጎታል፡፡

## በስጦታ መልክ ቅርሶች ወደ ውጪ ሀገር እንዳይሄዱ መከታተልን በተመለከተ

82. በስጦታ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄዱ እቃዎች ቅርስ አለመሆናቸው እና ቅርሶች ለንግድ ዓላማ እንዳይውሉ ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

83. በስጦታ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄዱ እቃዎች ቅርስ አለመሆናቸውን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ አልተገኘም፡፡ በስጦታ ዕቃ መሸጫ ሱቆች ውስጥ ከቅርስ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ዕቃዎች ሲሸጡ የተገኙበት ሁኔታ መኖሩን ከሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት ከተገኘ መረጃ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በስጦታ መሸጫ ሱቆች ላይ የሚደረገው ክትትል እና ቁጥጥር ደካማ መሆኑ ታውቋል፡፡

84. የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የንግድ ተቋማት የንግድ ፈቃድ የሚሰጠው የንግድ እና እንዱስትሪ ሚኒስቴር ሲሆን፣ ባለሥልጣኑ በዚህ ተግባር ላይ ተሳትፎ የሚያደርግበት ሁኔታ አለመመቻቸቱን፤ ሆኖም በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ወቅት የባለሥልጣኑን ተሳትፎ በተመለከተ ትኩረት እንዲሰጡት አስተያየት በባለሥልጣኑ ለንግድ ሚኒስቴር የተሰጠ መሆኑን እና ይህን ያካተቱት መሆኑን ግን እንደማያውቁ፤ በሌላ በኩል ግን ለነዚህ የንግድ ድርጅቶች ደረጃውን የጠበቀ እና የታወቀ አቅራቢ በሌለበት ሁኔታ በባህላዊ መንገድ የሚያመርቱ አቅራቢዎች ባሉበት ሁኔታ ይህንን ለመቆጣጠር ለባለሥልጣኑ አስቸጋሪ እንደሚሆን፤ በስጦታ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄዱ እቃዎችን በተመለከተ ወደ ውጪ የሚወጡትን ቅርሶች ለመከላከል ለጉምሩክ ባለሙያዎች ሥልጠና የሰጡ መሆኑን፣ ለወደፊት ቢያንስ የተመዘገቡ ቅርሶችን ለመቆጣጠር እንዲችሉ ኤሌክትሮኒክስ ኮድ (electronics code) በመስጠት እና ይህን መረጃ ከጉምሩክ ጋር በመለዋወጥ የተመዘገቡ ቅርሶች መጥፋትን ለመቀነስ በቀጣዩ አምስት ዓመታት ባለሥልጣኑ በእስትራቴጂ እቅድ የተያዘ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

85. ቅርሶችን መስለው ከሚሸጡ ዕቃዎች ጀርባ ትክክለኛ ቅርሶች ሊሸጡ የሚችሉበት ሁኔታ የሰፋ ከመሆኑም በላይ በስጦታ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄዱ እቃዎች ላይ የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት አለመኖር የቅርስን ጥፋት የሚያባብስ ይሆናል፡፡

## IV. የቅርስ ጥናትና ምርምር ፈቃድ አፈፃፀም ክትትልን በተመለከተ

### የአርኪዮሎጂ ጥናት ከሚያደረጉ አጥኚ ቡድኖች ጋር ከባለሥልጣኑ የሚላኩ ባለሙያዎች የመምረጫ መሥፈርትን በተመለከተ

86. የቅርስ ጥናት ከሚያደርጉ አካላት ጋር ከባለስልጣኑ የሚላኩ ባለሙያዎችን ለመምረጥ የሚያስችል የመምረጫ መስፈርት ሊኖር ይገባል፡፡

87. በአርኪዮሎጂ ቦታዎች ላይ የቅርስ ጥናት ከሚያደርጉ አካላት ጋር ከአርኪዮሎጂ ሙያ ጋር ተያያዥ ልምድ የሌለው ሠራተኛ የሚመደብበት ሁኔታ መኖሩን ከመረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለመጥቀስም ያህል አንድ ባለሙያ የማይዳሰሱ

ቅርሶች ተመራማሪ ሆኖ ሳለ ለአርኪዮሎጂ ጥናት ምርምር ከሚሄዱ ባለሙያዎች ጋር በአንቲኩቲ ኦፊሰርነት (antiquity officer) ተመድበው መሄዳቸውን ከደብዳቤ ቁጥር ቅጥም/22/15/2002 ላይ ከቅጥ-105 ተረድተናል:: በአርኪዮሎጂ ቦታዎች ላይ የቅርስ ጥናት ከሚያደርጉ አካላት ጋር ከባለስልጣኑ የሚላኩትን ባለሙያዎች (antiquity officer) ለመመደብ የሚቻልበት የመምረጫ መስፈርት እንዲቀርብ ተጠይቆ የሥራ መዘርዝር እንጂ የአመራረጥ መስፈርት አልቀረበልንም:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ በ2002 ዕቅድ ላይ በአርኪዮሎጂና ፖሊዮንቶሎጂ መመሪያ አማካኝነት የሚዘጋጁና ለመ/ቤቱ ባለሙያዎች ስለመስክ ክትትልና ቁጥጥር የሶስት ቀናት ሥልጠና እንደሚሰጥ በዕቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም በክንውን ሪፖርት ላይ ግን ይህ ሥራ ተግባራዊ ስለመሆኑ የቀረበ ሪፖርት አልተገኘም::

88. የአርኪዮሎጂ ጥናት ከሚያካሂዱ ቡድኖች ጋር የሚሄዱ ሠራተኞች ከአርኪዮሎጂ ጥናት ጋር ተያያዥ የሆነ ሙያ ከሌላቸው ወይም ተገቢው ሥልጠና ካልተሰጣቸው ተገቢውን የመስክ ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ አያስችላቸውም፡፡

## በቅርስ ላይ ጥናትና ምርምር ከሚያከናውኑ ባለሙያዎች የሚገኘው ገቢ ለቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ የሚውል መሆኑን በተመለከተ

89. ባለስልጣኑ ከቅርስ ጥናትና ምርምር ባለሙያዎች የጥናት ሥራ በፕሮጀክቱ ዋጋ ተመን መሠረት የሚገኘውን አስር በመቶ (10%) ገቢ ለቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ማዋል አለበት::

90. ከጥናትና ምርምር ባለሙያዎች ከሚገኘው አሥር በመቶ ገቢ ውስጥ ሃምሣ በመቶ ለቅርሱ ቦታ ማልሚያ እንዲውል መመሪያ ቢኖርም የደቡብ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የብዝሀ ባህል አስተባባሪ እንደገለፁት በክልሉ በቅርስ ዙሪያ ከሚከናወኑ የጥናት ሥራዎች የሚገኘው አስር በመቶ (10%) ገቢ በክልሉ ለሚገኙ የቅርስ ቦታዎች ማልሚያ መዋል ሲገባው ገቢው ለክልሎቹ የማይላክ እና ጠቅላላ የተሰበሰበው አስር በመቶ ባለስልጣኑ የሚያስቀርበት ሁኔታ እንዳለ አስረድተዋል፡፡

91. ይህን አስመልክቶ የቅርስ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ በቅርሶች ላይ ጥናት ከሚያደርገው ቡድን የሚሰበሰበው አስር በመቶ (10%) ለቅርሶች ጥበቃ ይውላል የሚል ቢሆንም፤ አጥኚዎቹ ክፍያውን ሳይፈጽሙ

የጥናት ፈቃድ እንዳይሰጣቸው ከመከታተል በዘለለ ይህ ገንዘብ ለምን ዓላማ እንደሚውል የሚያውቁት ነገር እንደሌለ፣ ይህን በተመለከተ የባለሥልጣኑን ሂሳብ ክፍልን መጠየቁ የተሻለ እንደሚሆን ገልጸዋል::

ይህንን ሁኔታ በተመለከተ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በቅርስ ላይ ጥናት ከሚያደርጉ የሚሰበሰበው አስር በመቶ በዓመት ከአንድ ሚሊየን የማይበልጥ ከመሆኑም በላይ በአጠቃላይ ቅርስን ከመጠበቅ ውጭ የሚከናወን የባለስልጣኑ ተግባር ስለሌለ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለቅርስ ጥበቃ እንደሚውል ገልጸዋል፡፡

92. ከቅርስ ጥናትና ምርምር የሚገኝ ገቢ ለቅርስ ጥበቃ፤ ጥገናና ልማት ካልዋለ በጥበቃና ጥገና እጦት ትልልቅ ቅርሶችን ሙሉ ለሙሉ ወደ ማጣት ሊኬዱ ይችላል፡፡

# V. ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን በተመለከተ

## ባለሥልጣኑ መ/ቤት እና በፌዴራል ደረጃ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የሥራ ድርሻ በግልጽ ተለይቶ መቀመጡን በተመለከተ

93. ቅርሶችን ከምዝበራና ከጥፋት ለመጠበቅ የባለስልጣኑ መ/ቤት እና በፌዴራል ደረጃ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ማንነት እና ሊኖራቸው የሚገባው የሥራ ድርሻ በጥናት ሊለይ እና ባለድርሻ አካላቱ እንዲያውቁት ሊያደረግ ይገባል፡፡

94. የሀገሪቱን ቅርሶች በአግባቡ ለመመዝገብ፣ ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብ እና ለማልማት እንዲቻል የባለድርሻ አካላት ዝርዝር በቅርቡ በተጠናው እና ወደ ትግባር በተገባው የመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ የተቀመጠ ቢሆንም የእያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ኃላፊነት እና ተግባር በጥናት በግልጽ ተለይቶ እንዲያውቁት አልተደረገም፡፡

95. ይህንንም በተመለከተ የሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሲገልፁ በቅርቡ ከደብረ ፀሐይ ቁስቋም ቅርስ ጠፍቶ የነበረ ሲሆን፣ በፖሊሶች ጥረት ከጠፉት ቅርሶች ውስጥ ስንክሳር ብቻ የተገኘ መሆኑን፣ በበየዳ እየሱስ፤ በእንዝራራ ተክለ ሐይማኖት፤ በማህደረ ስብሀት አልዋሬ ማርያም እና በሌሎች በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ውድና

ሊተኩ የማይችሉ ቅርሶች ጠፍተው ሪፖርት የተደረገ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ቅርሶች ጠፍተው መቅረታቸውን፤ ለዚህ እንደምክንያት ያቀረቡት የባለድርሻ አካላት ከቤተ ክህነት ጋር በተቀናጀ መልኩ የመሥራት ችግር በመኖሩ እንደሆነ ገልጸዋል።

96. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የብዝሀ ባህል አስተባባሪ ተቀናጅቶ ለመስራት ፍላጎት ቢኖርም በተወሰኑ ባለድርሻ አካላት በኩል በተለይም በሃይማኖት ተቋማት በኩል ተገቢው ትብብር የማይደረግ መሆኑን፣ ግንኙነት ማድረግ ላይ ክፍተቶች እንደሚታዩ፣ በክልሉ ሙዚየሞችን ለማቋቋም የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ በክልል ደረጃ ደንብ የወጣ ቢሆንም የባለሥልጣኑ አስተያየት ተጠይቆ በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ በክልል ደረጃ ቅርስን በተመለከተ ደንብ ማውጣት እንደማይቻል በሚል የተቀመጠ በመሆኑ ለማፀደቅና ሥራ ላይ ለማዋል ያልተቻለ መሆኑ ገልፀዋል።

በኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ምክትል ቢሮ ኃላፊና የባህል ዘርፍ ኃላፊ ከባለስልጣኑ ሙዚየሞችን ለማቋቋም ምንም ዓይነት ፈቃድ የማይጠይቁ መሆኑና እና የቅርስ ጥገና ለማከናወን በክልል ደረጃ በወጣ እና በጸደቀ አዋጅ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑን ገልጸዋል፣፣

97. ባለስልጣኑ በቅርስ ጥናት እና ጥበቃ ላይ ባለድርሻ አካላት ሊኖራቸው የሚገባውን የሥራ ድርሻ በጥናት ለይቶ ባለማሳወቁ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ አለመሥራቱ ያለበት የአቅም ውስንነትን ለማቃለል እና በቅርሶች ላይ እየደረሰ ያለውን ጥፋትና ምዝበራ ለማስወገድ ባለ ድርሻ አካላት የበኩላቸውን እንዳይወጡ ሊያደርግ ይችላል።

## በቅርሶች አመዘጋገብ፣ አጠባበቅ እና ጥገና ዙሪያ የባለሥልጣኑ እና የክልሎች የሥራ ድርሻ በግልፅ መቀመጡን በተመለከተ

98. በቅርስ አመዘጋገብ፣ አጠባበቅ እና ጥገና ዙሪያ ባለስልጣኑ እና ክልሎች ያላቸው የሥራ ድርሻ በግልፅ መቀመጥ አለበት።

99. በቅርስ አመዘጋገብ፣ አጠባበቅ እና ጥገና ዙሪያ የባለሥልጣኑ እና የክልሎች የሥራ ድርሻ በግልፅ ተለይቶ አልተቀመጠም። በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ምክትል ቢሮ እና የባህል ዘርፍ ኃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት

ምላሽ በክልሉ የመንግስት አስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ መሠረት የክልሉ የሥራ ድርሻ ቅርሶች የመመዝገብ፣ ደረጃ የመስጠት፣ የመጠገን እና ባህላዊና ታሪካዊ ቅርሶችን እና እሴቶች የመጠበቅ ሥራ እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡

100. በሌላ በኩል በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቋሚ ቅርስ ጥገና ባለሙያ ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በቅርስ አጠባበቅ ዙሪያ የባለስልጣኑ እና የክልሎች የሥራ ድርሻ በግልፅ አለመቀመጡን ገልጸዋል፡፡

101. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የጌድኦ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ለዞኑ ባለሙያዎች ቅርስን አስመልክቶ በክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በተሰጠው ስልጠና ላይ ክልሎች ቅርስን የማጥናት፤ የመመዝገብ፤ የመንከባከብ እና የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው የተገለጸላቸው ቢሆንም በጽሁፍ በግልፅ የተቀመጠ ኃላፊነት እንደሌለ ገልፀዋል፡፡ በዚሁ በደቡብ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የብዝሀ ባህል አስተባባሪ ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 92 ላይ መንግስትና ሕዝብ ቅርስን ይጠብቃሉ የሚል ቢሆንም በመንግስት በኩል እና በሕዝብ በኩል መከናወን ያለባቸው ተግባራት ተለይተው ባለመቀመጣቸው አፈፃፀም ላይ አስቸጋሪ ሁኔታ እንደፈጠረ ገልጸዋል፡፡

102. የባለስልጣኑ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ባለስልጣኑ የክልሎችን አዋጅ ተናቦ የሚያዘጋጅበት መንገድ ባለመመቻቸቱ በሀገሪቱ ያሉ ቅርሶች በአግባቡ ተመዝግበው ተጠብቀውና እንክብካቤ ተደርጎላቸው ለልማት የሚውሉበት መንገድ ይፈጠራል ብለው እንደማያምኑ ገልጸዋል፡፡

103. ባለስልጣኑ እና ክልሎች በቅርስ አመዘጋገብ፤ አጠባበቅ እና ጥገና ላይ ያላቸው የሥራ ድርሻ በግልፅ ባለመቀመጡ  በባለሥልጣኑ እና በክልሎች መካከል የተቀናጀ ሥራ ለማከናወን እንዳይቻል የሚያደርግ በመሆኑ በቅርሶች ዙሪያ ሊሠሩ የሚገቡ ሥራዎች በወቅቱ እንዳይሠሩ እና ባለቤት እንዲያጡ በማድረግ ለብልሽት እና ለጥፋት እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡

## ቅርስን በመጠበቅ ተግባር የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት  በጋራ እቅድ በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ

104. ቅርሶችን ከምዝበራና ከጥፋት ለመጠበቅ ባለሥልጣኑ ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሠራበትን እቅድ በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

105. ባለሥልጣኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የቅርሶችን ምዝበራና ጥፋት ለመከላከል በቅንጅት የሚሠራበት ሁኔታ ተመቻችቶ አልተገኘም፡፡ የባለስልጣኑ አዋጅ ቁጥር 209/92 አንቀፅ 45 ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ የቅርስ ዝርፊያ ለሚፈፅሙ ዘራፊዎች የተለያየ ቅጣት የተደነገገ ቢሆንም ይህ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡

106. የሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ በዞኑ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙ ውድና ሊተኩ የማይችሉ ቅርሶች ጠፍተው ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፣ በተለይም በቅርስ ላይ ስርቆት እና ምዝበራ የፈፀሙ ግለሰቦች በፖሊስና በህብረተሰቡ ትብብር ተይዘው ህግ ፊት ቢቀርቡም  በህግ አስፈጻሚ አካላት በኩል ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲያገኙ ስለማይደረግ የቅርስ ስርቆት መስፋፋትን ያስከተለ መሆኑን፤ በጉምሩክ በኩል ሲወጡ መተማ ላይ የሚያዙ ቅርሶችን በመረከብ በኩል የተሠራ ሥራ ቢኖርም በእቅድና በጥናት ላይ የተመሠረተ የቅንጅት ሥራ የማይሰራ መሆኑን አስረድተዋል፣፣ በመቀጠልም በሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት በጎንደር ደብረ ብርሐን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ከፖሊስ ጋር ያለው የሥራ ግንኙነት አጥጋቢ ነው የሚል ዕምነት እንዳላቸው ሆኖም በቅርስ ዘራፊዎች ላይ የሚታየው የፍርድ አሰጣጥ አስተማሪ ያለመሆኑ እና አጥፊዎች ወዲያውኑ የሚለቀቁበት ሁኔታ መኖሩን፤ በምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት በጣና ደሴት የሚገኙት የክብራን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም እና የኡራ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በጥበቃቸው ስር ላሉ ውድ ጥንታዊ ቅርሶች ጥበቃ የሚሆን የተሻለ ዘመናዊ መሳሪያ እንዲሰጣቸው ቢጠይቁም ለረጅም ጊዜ ምላሽ እንዳልተሰጣቸው ገልጸዋል፡፡

107. የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የቅርሶች መጥፋትን እና ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ ያለመወሰድን በተመለከተ ቅርስን በአጠቃላይ መጠበቅ ያለባቸው ሁሉም የመንግስት አካላት እና ኅብረተሰቡ መሆናቸውን፤ ባለሥልጣኑ በዋነኛነት ሊሠራ የሚችለው የቅርስ ዋጋ (value) በኅብረተሰቡም ሆነ በሚመለከታቸው አካላት በኩል እንዲታወቅ እና ተገቢው ቦታ እንዲሰጠው ለማድረግ

የሚያስችል ግንዛቤ መፍጠርን እንደሆነ እና በተቻለ አቅም  የቅርስ ዋጋን በተመለከተ ግንዛቤ ለመፍጠር የተሞከረ ቢሆንም በባለድርሻ አካላት የሚገኙ ሥልጠናውን የወሰዱ ባለሙያዎች ሥራ በተደጋጋሚ የሚለቁበት ሁኔታ በስፋት በመታየቱ በዚህ ዙሪያ የተደረገው ጥረት ብዙም ውጤታማ አለመሆኑ፤ ይህን ችግር ለማቃለል እንዲቻል በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ትኩረት ተሰጥቶት በአሁኑ ወቅት  የመንግሥት ጠንካራ አስፈፃሚ አካል በሆኑት ወረዳዎች ላይ የተጠናከረ ሥራ ለመሥራት እና የቅርሱ ቀጥተኛ ባለቤቶች የሆኑትን አካላት በማግኘት በየክልላቸው ያሉ ቅርሶችን ተገቢውን ዋጋ (value) እንዲሰጡ እና እንዲጠብቁ ለማድረግ ዕቅድ መያዙን ገልጸዋል፡፡

108. ቅርስ የአንድ ሀገር ልዩ መገለጫ ሆኖ ሳለ እንደቀላል ጉዳይ መታየቱ እና ተገቢውን ዋጋ እንዲያገኝ አለመደረጉ ለምዝበራና ለጥፋት እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡  ቅርሶች ለምዝበራና ለጥፋት የሚጋለጡበትን ሁኔታ ለመቀነስ ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ወጥ የሆነ መርሐ ግብር ነድፎ በጋራ ባለመስራቱ እና የቅርስ ጥፋትና ምዝብራ ለሚፈፅሙ ዘራፊዎች በአዋጅ ላይ የተለያየ ቅጣት የደነገገ ቢሆንም ተግባራዊ ባለማድረጉ የቅርስ ዝርፊያ ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ እንዲሄድ አድርጎታል፡፡ ለሚሰረቁና ለሚዘረፉ ቅርሶች ተገቢው ሕጋዊ ክትትል በማድረጉ ረገድ ድክመት የሚታይ በመሆኑ ቅርሶች በቀላል ጥቅም ከሀገር የሚወጡባቸው መንገዶች በስፋት እንዲፈጠሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በቅርስ ጥበቃ ሥራ ላይ የተሠማሩ ግለሰቦች የሚይዙት መሳሪያ ኋላቀርና ያረጀ መሆን የቅርስ ስርቆት ተግባርን የሚፈጽሙ ዘራፊዎች በቀላሉ በማጥቃት የቅርስ ዘረፋ እንዲበራከት መንገድ ይከፍታል፡፡

## ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ መ/ቤቶች ተቀናጅተው የሚሠሩበት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

109. ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተጠሪ ከሆኑ መ/ቤቶች ጋር በጋራ ሊሠሩ የሚገባቸው ሥራዎች በተቀናጀ ሁኔታ  ለመሥራት የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡

110. በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ስር ከሚገኘው ከዱር እንስሳት ባለስልጣን ጋር ባለስልጣን መ/ቤቱ ተቀናጅቶ የሚሰራበት ሁኔታ አልተመቻቸም፡፡ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ ባለስልጣኑ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ስር ካሉ መ/ቤቶች ጋር በተወሰነ መልኩ የሚያገናኛቸው ዓላማ ያለ እና

ይህንን ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ተቀናጅቶ መሥራት አስፈላጊነቱ የሚታመንበት ቢሆንም በዚህ ረገድ የተከናወነ ተግባር እንደሌለ ገልፀዋል፡፡ በማያያዝም የቅርስ የሥራ ባሕርይ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በተለይም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ ከሆኑት አካላት ጋር በጋራ ተቀናጅቶ መሥራት አስፈላጊ መሆኑን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አዲስ የተቋቋመው የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን ስላመነበት በራሱ ተነሳሽነት ግንኙነት ለማድረግ እየሞከረ ያለበት ሁኔታ መታየቱ ጥሩ ጅምር መሆኑ፣ ሆኖም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህን ተግባር ትኩረት ሊሰጠው እና አጠናክሮ ሊያከናወን እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

111. በባለሥልጣን መ/ቤቱ እና በባህልና ቱሪዝም ሚ/ር ስር ያሉ መ/ቤቶች የሚያከናውኑቸው ተግባሮች ተያያዥነት ያላቸው ከመሆኑ አንፃር የጋራ ዓላማቸውን ለመወጣት በተቀናጀ መልኩ አብሮ የመሥራት ሁኔታ አለመኖሩ ዓላማቸውን በብቃት ለማሳካት እንዳይቻል ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

## በባለሥልጣኑ ለክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች በቅርስ ዙሪያ የሚያደርገውን የሙያ ድጋፍ በተመለከተ

112. ባለስልጣኑ ለክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች በየደረጃው በቅርሶች ዙሪያ ለሚደረጉ ማንኛውም ሥራዎች የሙያ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

113. በባለሥልጣኑ ለክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች በየደረጃው በቅርሶች ዙሪያ ለሚደረጉ ማንኛውም ሥራዎች የሙያ ድጋፍና ስልጠናዎች በተሟላ መልኩ የሰጠበት ሁኔታ አልታየም፡፡ በአማራ ክልል የሚገኙ ቅርሶች የሚገኙባቸው አብያተ ክርስቲያናት እና የሀገረስብከቱ የሥራ ኃላፊዎች በቅርስ አጠባበቅ ዙሪያ ስልጠና ያልተሰጠ እና ልምድ ያለው ባለሙያ አለመመደቡን፣ በዚህ ዙሪያ ስልጠና ማግኘቱ አስፈላጊ መሆኑን እንደሚያምኑበት ሆኖም በቅርስ ዙሪያ ስልጠና ለሚሰጡ አካላት ተገቢው መስፈርት ሊቀመጥና ቅርሱን በቀጥታ ለሚጠብቁ አካላት ትኩረት ቢሰጥ የተሻለ እንደሆን ገልጸዋል፡፡

114. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቋሚ ቅርስ ጥገና ባለሙያ በክልሉ በቅርስ ጥገና ዙሪያ በሙያው ልምድና ብቃት ያለው የሰው ኃይል አለመሟላቱን፣ ያሉትን ባለሙያዎች ለማብቃትም የሚሰጠው ሥልጠና የተጠበቀውን

ያህል ውጤታማ እንዳልሆነ እና ድክመት እንደሚታይበት፤ በክልሉ የሚገኘውን የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት የሚቀርፉ መሠረታዊ ስልጠናዎች በተለይ ረጅም ጊዜ የሚጠይቁ እና ቅርሶችን በአግባቡ ለመጠበቅ የሚረዱ ስልጠናዎች ወደ ክልል እንደማይደርሱ፤ በተጨማሪም በክልል ደረጃ በቋሚ ቅርሶች ጥገና ላይ ልምድ ያላቸው ሁለት፤ ልምድ የሌላቸው ሁለት በጠቅላላው አራት ባለሙያዎች ብቻ ያሉ መሆኑን፤ በተንቀሳቃሽ ቅርሶች ላይ ግን የጥገናና የቁጥጥር ባለሙያ አለመኖሩን፤ በመሆኑም እነዚህን ቅርሶች በአግባቡ ለማደራጀትና ለመጠበቅ የሚያስችል ስራ እየተሰራ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

115. የሰሜን ጎንደር ዞን የባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ በዞኑ የሚገኙ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን ለመጠገን ብቃት ያለው የጥገና ባለሙያ ድጋፍ ጠይቀው ለማግኘት እንዳልቻሉ፤ በዞኑ የሚገኙ ቅርሶች በተለይም ቋሚ ቅርሶችን ለመጠበቅና ለመንከባከብ በሙያው ልምድና ብቃት ያለው የሰው ኃይል እንዳልተሟላ እና የሚያስፈልጉ ባለሙያዎች አይነት እና ብዛት በአግባቡ ተጠንቶ አለመቀመጡን፤ ቀደም ሲል በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የተሻለ ስልጠና ይሰጥ የነበረ ቢሆንም ከጊዜ በኋላ የተዳከመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

116. በኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ምክትል ቢሮ ኃላፊና የባህል ዘርፍ ኃላፊ በቅርስ ዙሪያ ለሚከናወኑ ተግባራት በሙያው ልምድና ብቃት ያለው የሰው ኃይል እንዳልተሟላ፤ ባለሙያዎችን ለማፍራትም አግባብነት ያለው ሥልጠና አለመኖሩን፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን መቀሌና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲዎች በቅርስ ጥበቃ ዙሪያ የትምህርት ክፍል ተቋቁሞ ሥልጠና መስጠት መጀመራቸው አበረታች መሆኑን ሆኖም የሚታየውን የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ለማቃለል አሁንም ሰፊ ጥረት መደረግ እንዳለበት የገለጹ ሲሆን፣ በዚሁ ክልል የባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በዞኑ በሙያው ልምድና ብቃት ያለው የሰው ኃይል እንዳልተሟላ እና በቅርስ አጠባበቅ ዙሪያ ተያያዥነት ያለው ባለሙያ እጥረት መኖሩን እንዲሁም በቢሮው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሙያው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ባለሙያዎች ከአምስት እንደማይበልጡ ገልጸዋል፡፡

117. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የብዝሀ ባህል አስተባባሪ በተለያዩ የቅርስ ኤክስፐርቶች በክልሉ ውስጥ በሚደረጉ ጥናቶች ላይ

በክልሉ የሚገኙ የቅርስ ባለሙያዎች ልምድ ሊያገኙ ሲገባ በቀጥታ ከባለስልጣኑ የመጡ ባለሙያዎች ብቻ ይህን እድል የሚያገኙበት ሁኔታ እንደሚታይ፤ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ተመርቀው በቅርስ ዙሪያ በሚከናወኑ ተግባራት ላይ በክልሉ ለሚሰማሩ ባለሙያዎች ቅርስን በተመለከተ ተገቢው የማስተዋወቂያ ሥልጠና ሊሰጣቸው የሚገባ ቢሆንም በባለስልጣኑ በኩል እገዛ ተደርጎ ሥልጠና እንዲያገኙ ሳይደረግ ወደ ሥራ ቀጥታ እንደሚሰማሩ ገልጸዋል፡፡ በዚሁ ክልል የጌድኦ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች አዲስ ለተቀጠሩ ባለሙያዎች በቋሚ ቅርሶች ጥገና እና በአጠቃላይ በቅርስ አጠባበቅ ዙሪያ የአሠራር ስልጠና እንዲያገኙ መደረግ፤ በክልሉ ስለሚገኙ ቋሚ ቅርሶች (ትክል ድንጋይ) ምንነት ግልፅ የሆነ መረጃ የሚሰጥ ጥናት ማከናወን፤ የተለያዩ የውጪ የቅርስ ባለሙያዎች የሚያጠኑትን ጥናት የዞኑ ባለሙያዎች ሊረዱ በሚችሉት ቋንቋ የማዘጋጀት ተግባራት ሊከናወኑ የሚገባ ቢሆንም፣ የባለስልጣኑም ሆነ የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ድጋፍ በጣም ደካማ በመሆኑ በቅርስ አጠባበቁ ላይ ተጽዕኖ እያስከተለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የጉራጌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች በቅርስ አጠባበቅ ዙሪያ የሚሰጡት ሥልጠናዎች ከቅርስ ጥበቃ ሥራው ጋር ተያያዥና ቀጣይ ሆነው የሚሰጡበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡ የክልሉ ፖሊስ ቀርቦለት በሞላው መጠይቅ ላይ ለፖሊስ አባላት ከቅርስ ጥበቃ ጋር በተያያዘ ስልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

118. የአዲስ አበባ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ እና በአስተዳደሩ የባሕል እና ቱሪዝም ቢሮ ባለሙያዎች ከቅርስ ጋር የተያያዘ ሙያዊ ስልጠና በባለስልጣኑ በኩል እስካሁን እንዳልተሰጠ አስረድተዋል፡፡

119. በባለስልጣኑ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት የትግበራ መርሐ ግብር ላይ ቅርስ ጥበቃን አስመልክቶ አጫጭር ሥልጠና በዓመት አራት ጊዜ ለአሥር ቀናት እንደሚሰጥ የተቀመጠ ቢሆንም ትግበራው ከተጀመረ ጀምሮ ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ በአካል በጎበኘናቸውም ሆነ መጠይቅ ባቀረብንላቸው ክልሎች ምንም አይነት እንቅስቃሴ አልተደረገም፡፡

120. የባለሥልጣኑ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በቅርስ አጠባበቅ ጥገናና እንክብካቤ ዙሪያ የአሰልጣኞች

ስልጠና በተወሰነ ደረጃ የሚሰጡ ቢሆንም ይህን ግንዛቤ ወደታች የማውረድ ችግር እንዳለ ገልፀዋል፡፡

121. በሃይማኖት ተቋማት ያሉ ውድና ልዩ የሆኑ ቅርሶች ለመጠበቅ የሚመደቡት ሠራተኞች በሙያው ስልጠና የሌላቸው መሆኑ ቅርሶችን ለመጠበቅና ለመንከባከብ በቂና ተያያዥ የሆነ ሥልጠና ወጥ በሆነ መልኩ ከክልል ጀምሮ በየደረጃው ዞን እና ወረዳ ድረስ አለመስጠት በቦታው የተመደቡ ሠራተኞች እውቀታቸው እንዳይሻሻል ግንዛቤአቸው እንዳይዳብር ያደርጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቅርሶች በቂ እውቀት በሌላቸው ሠራተኞች አግባብ ባለው መንገድ ባለመቀመጣቸው እና ባለመጠበቃቸው የመበላሸትና የመጥፋት እድል ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡

## በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ሊጠበቁ የሚገባቸው ቅርሶች ደረጃ ማውጣትን በተመለከተ

122. የሀገሪቱን ቅርሶች በአግባቡ ለማስተዳደር እና ለመጠበቅ በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ሊተዳደሩና ሊጠበቁ የሚገባቸው ቅርሶች ደረጃ ሊወጣ ይገባል፡፡

123. ባለሥልጣኑ አዘጋጅቶ ያቀረበው የቅርሶች ደረጃ ምደባ ደንብ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ወቅት ድረስ ያልጸደቀ መሆኑ ታውቋል፡፡ በባህልና ቱሪዝም ሚ/ር የ2001 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በባለሥልጣኑ በአዲስ መልኩ የተቀረፀው የቅርስ ደረጃ ምደባ ደንብ መስፈርቶችን ማሻሻያ እና የማስፈፀሚያ መመሪያ እንዲጸድቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የቀረበ ቢሆንም ባለመፅደቁ የቅርስ ደረጃ ማውጣት ተግባር እንዳልተከናወነ ተገልጿል፡፡

124. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ምክትል ቢሮ ኃላፊ እና የባህል ዘርፍ ኃላፊ ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በአዋጁ ላይ የቅርሶች ደረጃ የማውጣት ሥራ በህግ እንደሚወሰን ቢገለጽም ይህን በተመለከተ በባለስልጣኑ ምን ተግባር እንደተከናወነ የሚታወቅ ነገር እንደሌለ፤ ሁኔታው አሳሳቢ በመሆኑ ባለሥልጣኑ ሳያሳውቅ እና ሳያስፈቅድ በራሱ ተነሳሽነት በክልሉ የቅርስ ደረጃ ማውጣት ተግባር በተለምዶ አሠራር የቅርሱን አስፈላጊነት ግምት ውስጥ በማስገባት እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

125. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቋሚ ቅርስ ጥገና ባለሙያ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ በሆነ መልኩ የቅርስ ደረጃ ማውጣትም ሆነ ተያያዥ ሥራዎች ሊሠሩ የሚቻልበት ሁኔታ ካልተመቻቸ በተናጠል መሥራቱ ተገቢ አለመሆኑን እና በቅርስ አጠባበቅ ላይም ጎጂ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

126. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የብዝሀ ባህል አስተባባሪ የደረጃ ማውጣት ሥራ ሕጉ ስላልወጣ በክልሉ የቅርስ ደረጃ ማውጣት ሥራ እንዳልተጀመረ ገልጸዋል፡፡

127. የባለስልጣኑ የቅርስ ኢንቬንቶሪ፣ ቁጥጥርና ደረጃ ማውጣት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ ባለስልጣኑ አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል እንዲፀድቅ ያቀረበው የቅርሶች ደረጃ ምደባ ደንብ በየደረጃው የሚገኙ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን በግልጽ በመረዳት የሀገሪቱን ቅርሶች በአግባቡ ለመጠበቅ እንዲችሉ ለማድረግ ካለው ከፍተኛ ጠቀሜታ አንፃር ትኩረት እና ቅድሚያ በመስጠት ፀድቆ ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ ሊፈጠር እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

128. የቅርስ የደረጃ ምደባ ደንብ ፀድቆ ባለመውጣቱ እና የቅርሶች ደረጃ ባለመለየቱ በፌዴራል፤ በክልል፤ በዞን ወዘተ… በየደረጃው የሚገኙ የቅርስ ባለቤቶች ያለባቸውን የስራ ድርሻ ኃላፊነት እንዲያውቁት ባለማድረጉ ቅርሶችን የመጠበቅና የመንከባከብ ተግባር በየደረጃው ባሉ አካላት በብቃት እንዳይከናወን እና ተጠያቂነት እንዳይጠናከር አድርጓል፡፡

## የልማት ሥራዎች በሚከናወኑበት ወቅት በቅርሶች ላይ ጉዳት እና ጥፋት እንዳይደርስ የማዳን ሥራ የሚከናወን መሆኑን በተመለከተ

129. የልማት ሥራ ሲከናወን በቅርስ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የማዳን ሥራ ማከናወን አለበት፡፡

130. የልማት ሥራ ከመሠራቱ በፊት በቅርስ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በባለስልጣኑ በኩል የቅርስ ማዳን ሥራ እንደማይሠራ ታውቋል፡፡ ይህም በመሆኑ በኦሮሚያ ክልል በመልካ ዋከና ግድብ የሰርቬይ ስራ

ሳይሰራ በመቅረቱ ገደብ አሳሳን የመሰሉ የቅድመ ታሪክ ቅርሶች መረጃ ሊያዙ እና ሊጠበቁ እንዳልቻሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የብዝሀ ባህል አስተባባሪ ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የተለያዩ የልማት ሥራዎች በሚሠሩበት ወቅት የተፅዕኖ ግምገማ (Impact assessment) እንደማይከናወን ገልፀዋል፡፡

131. የባለስልጣኑ የጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የግልገል ጊቤ ሁለት እና ሶስት ፕሮጀክት ላይ የተፅዕኖ ግምገማው (Impact assessment) በአካባቢው ባሉ ቅርሶች ላይ ተጨማሪ ጥናት ማድረግ ይጠቅም ስለነበር ተጨማሪ ጥናት መደረጉን፣ ሌሎች ፕሮጀክቶች ላይ ግን የተጠኑት የተፅዕኖ ግምገማ ጥናቶች ቅርሶችን ለስጋት የሚዳርጉ ባለመሆናቸው ተጨማሪ ጥናት እንዳላስፈለገ ገልፀዋል፡፡

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የአካባቢ የስጋት ግምገማ (Enviromental impact assessment) አሠራር ሥርዓት የተዘረጋ እና በአዋጅ የጸደቀ ቢሆንም በህብረተሰቡም ሆነ በአንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናት በኩል ስለ ቅርስ ያለው አመለካከት ዝቅተኛ በመሆኑ እና ማስፈፀሚያ የሚሆን በጀት ባለመመደቡ ተግባራዊ በማድረጉ ረገድ የጎላ ድክመት እንደሚታይ እና ቀልጠፋና አመርቂ የሆነ ተግባር እንዳልተከናወነ ገልፀዋል፡፡

132. ማንኛውም የልማት ሥራ ከመካሄዱ በፊት በቅድሚያ የቅርስ ማዳን ስራ የአካባቢ የስጋት ግምገማ (Enviromental impact assessment) ሊከናወን ካልቻለ ያልታወቁ እና የጎላ ጠቀሜታ ሊኖራቸው የሚችሉ በርካታ ቅርሶች ሊወድሙ ይችላሉ፡፡

# VI. በቅርስ ጥበቃ እና እንክብካቤ ዙሪያ የተመደበ የሰው ኃይልን በተመለከተ

## የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች የሥነ ምግባር ደንብን በተመለከተ

133. በቅርስ ጥበቃ ጥገናና እንክብካቤ ሥራ ላይ ለሚመደቡ ሠራተኞች ከሀገሪቱ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ የሥነ ምግባር ደንብ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

134. በቅርስ ጥገና፣ ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ላይ የተመደቡ ባለሙያዎች የስነምግባር ደንብ ከሀገሪቷ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ ያልተዘጋጀበት ሁኔታ አንዳለ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ገልፀዋል፡፡

135. የቅርስ ጥገና እና እንክብካቤ ለሚያደርጉ ባለሙያዎች የሚሆን የሙያ ስነ ምግባር ደንብ የባለስልጣኑን እና የሀገሪቷን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ያለመዘጋጀቱ ባለሙያዎቹ ተጠያቂነት የሰፈነበት ሥራ እንዳይሠሩ ያደርጋቸዋል፡፡

## የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ ባለሙያ መመደቡን በተመለከተ

136. በባለሥልጣኑ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት መሰረት ለቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ /የጥበቃና እንክብካቤ ጥናትን ሳይጨምር/ 33 ፈፃሚዎች የሚያስፈልጉ ቢሆንም 20 የሥራ መደቦች ክፍት ሆነው የሰው ኃይል ሳይመደብባቸው ተገኝቷል፡፡

137. በናሙና ተለይተው በታዩ ክልሎች፤ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፤ የጌዲኦ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ በሰጡት አስተያየት ቅርስን በመጠበቅ ዙሪያ በታሪክ፤ በአንትሮፖሎጂ፤ በአርኪሎጂ፤ በሶሾሎጂ፤ በጂኦግረፊ እና በዲሞግራፊ የሠለጠኑ ባለሙያዎች የሚያስፈልጉ ቢሆንም ያሉት ባለሙያዎች ግን አንድ በታሪክና አንድ በአንትሮፖሎጂ ሙያ የሰለጠኑ ብቻ በመሆናቸው በቅርስ ጥበቃ ዙሪያ ከፍተኛ የባለሙያ እጥረት እንዳሚታይ ገልፀዋል፡፡ የጉራጌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት ለዚህ ሥራ 27 ባለሙያ እንደሚያስፈልግ የተቀመጠ ቢሆንም የተመደበው የሰው ኃይል ግን 15 ብቻ በመሆኑ 12 ክፍት የሥራ መደቦች መኖራቸውን ገልፀዋል፡፡

138. በኦሮሚያ ክልል በባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በቅርስ ዙሪያ ለሚከናወኑ ተግባራት 19 ባለሙያዎች የሚያስፈልጉ ቢሆንም 11 ብቻ የተመደቡ እና ከነዚህ ውስጥ 6ቱ ከሙያው ጋር ተያያዥነት ያለው ትምህርትና ልምድ የሌላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

139. በዞን፤ በወረዳ እና በክልሎች እንዲሁም በባለሥልጣኑ በቅርስ ጥገና፤ ጥበቃ እና እንክብካቤ ተግባር ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎች በበቂ ሁኔታ ያልተሟላ መሆኑ በቅርሶች ላይ ተገቢው ሥራ እንዳይከናወን ያደርጋል፡፡

## VII.ቅርስን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ ሥርዓትን በተመለከተ

### የተመዘገቡ ተንቀሳቃሽና ቋሚ ቅርሶች የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን በተመለከተ

140. የተመዘገቡ ተንቀሳቃሽና ቋሚ ቅርሶችን መረጃ በአግባቡ ሊያዝ ይገባል፡፡

141. ቅርስ የሚገኝባቸው የዕምነት ቦታዎች ያላቸውን የቅርስ ብዛት በውል የማይታወቅ ሲሆን፣ መረጃቸው በአግባቡ ተይዘው አልተገኘም፡፡ ለመጥቀስ ያህልም በአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቋሚ ቅርስ ጥገና ባለሙያ በክልሉ ያሉትን ቋሚ፤ ተንቀሳቃሽና የማይዳሰሱ (intangable) ቅርሶች በቁጥር ለመግለፅ አስቸጋሪ መሆኑን፣ በክልሉ ያሉት ቅርሶች በሙሉ ተጠንተውና ተመዝግበው ተይዘዋል ማለት የማይቻል መሆኑን፡ የተመዘገቡትም ቢሆን ተገቢውን የቅርስ አመዘጋገብ መስፈርት ጠብቀው ተመዝግበዋል ለማለት እንደማይቻል ገልፀዋል፡፡ ባለሙያው ይህን የገለጹ ቢሆንም በአገር አቀፍ ደረጃ ቅርሶችን ወጥ በሆነ መልኩ የቋሚ ቅርሶች አመዘጋገብ መስፈርት አላስቀመጠም፡፡ በክብራን ቅዱስ ገብርኤል ሙዝየም ጠባቂና አስጎብኝ በቅርስ ምዝገባና ቆጠራ ጊዜ ባህልና ቱሪዝም ቅርሶቹን ሲመዘግብ የቅርሶችን ሁኔታና ምንነት ገላጭ በሆነ መልኩ የማይፃፍና ጠቅላላ የቅርሶቹ ብዛት ምን ያህል እንደሆነ በቃል እንደማያውቁ ግን በመዝገብ ላይ ተመዝግበው እንደሚገኙ ምላሽ የሰጡ ቢሆንም ቅርሶቹ የተመዘገቡበት መረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

142. የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ቅርስ ምዝገባን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ በጣና ደሴቶች ውስጥ ባሉ ገዳማት ውስጥ ከ1270 ዓ.ም ጀምሮ ያሉ ብዛት ያላቸው ውድ ቅርሶች የተመዘገቡ መሆኑን እና እዚያው ባሉበት ገዳምም ሆነ በሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት እንዲሁም በየወረዳ የቤተ ክህነት ጽ/ቤቶች መረጃቸው የሚያዝ እና በቅርሶች ምዝገባ ወቅት አንድ ቅጅ ለአጥቢያው፣ አንድ ቅጅ ለሀገረ ስብከቱ፣ ሶስተኛው ደግሞ ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን እንደሚሰጥ የገለፁ ቢሆንም እነዚህን መረጃዎች በተገለጸው ሁኔታ ተይዘው አልተገኙም፡፡

143. ይህ ሁኔታ የተመዘገቡ ተንቀሳቃሽና ቋሚ ቅርሶችን መረጃ ሊይዙ የሚገባቸው አካላት በሙሉ በቅጅ እንዲደርሳቸው አለመደረጉን እና መረጃውን በአግባቡ ሊይዙ የሚችሉበት ሁኔታ አለመመቻቸቱን ያሳያል፡፡

## በባለሥልጣኑ የቅርስ ምዝገባን ሥራ በማዕከል ደረጃ በዳታ ቤዝ የተያዘና ከክልሎች ጋር በኔትወርክ የተገናኘ መሆኑን በተመለከተ

144. በባለሥልጣኑ የሚከናወን የቅርስ ምዝገባ ሥራ በማዕከል በዳታ ቤዝ ተይዞ ከክልሎች ጋር በኔትወርክ የተገናኘ እና መረጃዎችን በቀላሉ ለመለዋወጥ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

145. ክልሎችን ከባለስልጣኑ የመረጃ ቋት ጋር የማገናኘት ተግባር ለማከናወን የተቀረጸው ፕሮጀክት በቅርስ ኢንቬንቶሪ፣ ቁጥጥር እና ደረጃ ማውጣት ዳይሬክቶሬት እና በኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርስ ፕሮጀክት አማካኝነት የሚተገበር መሆኑ በ1999 በጀት አመት እቅድ ላይ የተገለፀ ቢሆንም ፕሮጀክቱ አሁን ስላለበት ሁኔታ የቅርስ ኢንቬንቶሪ፣ ቁጥጥር እና ደረጃ ማውጣት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርሶች ፕሮጀክት ለባለስልጣኑ በምን መልኩ ሥራውን አስረክቦ እንደወጣ እንደማያውቁ ገልፀዋል፡፡ በ1999 ዓ/ም ዓመታዊ የድርጊት መርሐ ግብር ላይ ከኢትዮጵያ የባህል ቅርስ ፕሮጀክት ጋር በመተባበር የባለስልጣኑን የመረጃ ማዕከል ከአማራና ከትግራይ የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች በማገናኘት የኮምፒውተር ኔትወርክ መዘርጋትና መረጃዎችን ማደራጀት የሚል እቅድ የተቀመጠ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ላይ በ23 ባለሙያዎች በመቀሌ፤ አክሱም፤ ጎንደር እና ባህርዳር በሁለት ወራት 1246 ቅርሶች በሀርድ ኮፒና (hard copy) በአካባቢው ባለ እና በተወሰነ ኔትወርክ ወደ ዳታ ቤዝ ከመግባቱ ውጪ የባለስልጣኑን የመረጃ ማዕከል ከነዚህ ቦታዎች የመረጃ ማዕከል ጋር የማገናኘት ተግባር ስለመከናወኑ የተገለጸ ነገር የለም፡፡

የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ኤጀንሲ እና የድሬዳዋ አስተዳደር ንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ቅርስን በተመለከተ በተላከላቸው መጠይቅ ላይ በየክልሉ ያሉና የተመዘገቡ ቅርሶች መረጃ በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን እንደማይገኝ ገልፀዋል፡

146. ክልሎች ከባለስልጣኑ የመረጃ ቋት ጋር በኔት ወርክ ባለመገናኘታቸው ባለስልጣኑ የቅርሶችን ደህንነት ለመከታተልና ለመቆጣጠር አያስችለውም፡፡ እንዲሁም የመረጃ ልውውጥንና ፍሰቱን የተቀላጠፈና ዘመናዊ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡ ከዚህም ባሻገር የቅርሶች ምዝገባ ላይ የድግግሞሽ ስራ እንዲሰራ በር ይከፍታል፡፡

## የቅርስ መረጃዎችን በድረ ገጽ እና በተለያዩ ማሰራጫ መንገዶች ለማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

147. የተለያዩ የቅርስ መረጃዎችን በድረ-ገፅ በህትመት፤ በፖስተር፤ በመፅሄትና በሌሎች አመቺ መንገዶች ማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

148. የሰሜን ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ፤ የጌዲዮ እና የባሌ ዞኖች ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤቶች በፌዴራል ደረጃ ቅርስን በሚመለከት የተዘጋጁ ጥናቶች፣ ብሮሽሮች፣ መጽሔቶች ወዘተ እንደማይደርሳቸው የገለጹ ሲሆን፣ በኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ምክትል ቢሮ ኃላፊና የባህል ዘርፍ ኃላፊ እንዲሁም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቋሚ ቅርስ ጥገና ባለሙያ የሚላክላቸው የመጽሔቶች፤ የብሮሽሮች እና የጥናቶች ብዛት ክልሉ ካለው የዞንና የወረዳ ቁጥር ጋር የማይመጣጠን በመሆኑ ለሁሉም ለማዳረስ እንዳልተቻለ ገልፀዋል፡፡

149. የድረ-ገፅን በሚመለከት ባለስልጣኑ እስካሁን የተደራጀ የድረ-ገፅ እንደሌለው ተረድተናል፡፡ ይህንንም በተመለከተ የባለስልጣኑ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና የመረጃ ስርዓት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው ከሶስት ወራት በኋላ እንደሚቋቋም ገልፀዋል፡፡

150. በሀገር አቀፍ ደረጃ የተደራጀ እና የቅርስ መረጃዎችን በብቃት ለመለዋወጥ የሚያስችል የድረ-ገፅ አለመኖር ቅርሶችን በአግባቡ መዝግቦ ለመያዝ፣ ለመጠበቅ እና ለማስተዋወቅ እንዲሁም ቅርስ ነክ መረጃዎችን ለሚፈልጉ አካላት የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት አያስችልም፡፡

## በባለሥልጣኑና በሁሉም ባለድርሻ አካላት መካከል የቅርስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ

151. በቅርሶች ዙሪያ ለሚከናወኑ ሥራዎች በሁሉም ባለድርሻ አካላት እና በባለስልጣኑ መካከል የመረጃዎች ልውውጥ ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

152. በባለሥልጣኑና በሁሉም ባለድርሻ አካላት መካከል ያለው የመረጃ አያያዝ እና ልውውጥ ሥርዓት አጥጋቢና ዘመናዊ ባለመሆኑ ባለሥልጣኑ ቅርስን የተመለከቱ መረጃዎች በተሟላ ሁኔታ አይደርሰውም፡፡

153. የኦዲት ቡድኑ ባደረገው የመስክ ጉብኝት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ምክትል ቢሮ እና የባህል ዘርፍ ኃላፊዎች የቅርስ ምዝገባን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራትን ለባለስልጣኑ ለማሳወቅ ጥረት የሚያደርጉ ቢሆንም የመረጃ ልውውጡ ድክመት የሚታይበት በመሆኑ የቅርስ ምዝገባ ድግግሞሽ ሊፈጠር እንደሚችል፤ በተጨማሪም በክልሉ ከሚገኙ የሃይማኖት ተቋማት፤ ከፖሊስ፤ ከባህላዊ መሪዎች፤ ከፍርድ ቤቶች እና ከአቃቢ ሕግ ጋር ያለው ግንኙነት ደካማ መሆኑን፤ ከክልል ጀምሮ በየደረጃው ቅርስን አስመልክቶ በሚከናወነው ሥራ ላይ ሰፊ እና የጎሉ ችግሮች የሚታዩ መሆኑንና በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በኩል ቅርስን በተመለከተ ለህዝብ ተወካዬች ምክር ቤት የሚቀርበው ሪፖርት ላይ እነዚህ ችግሮች መኖራቸው እንደማይገለጽ አስረድተዋል፡፡

154. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በጉራጌ እና የጌዲኦ ዞኖች ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች የባህልና ቱሪዝም መዋቅር ወረዳ ድረስ ባለመውረዱ ለባህልና ቱሪዝም ዘርፍ በተለይም በቅርስ ዙሪያ ሊከናወኑ ለሚገባቸው ተግባራት ተገቢው ትኩረት ለመስጠት አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

155. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ኤጀንሲ በክልሉ የሚገኙ የተመዘገቡ ቅርሶች መረጃዎችን ለክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፤ ለዞኑ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ፤ ለወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት እና ቅርሱ ለሚገኝበት ቦታ በቅጅ እንደሚልኩ ገልፀዋል፡፡ በድሬዳዋ አስተዳደር ንግድና ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮም የቅርስ መረጃዎችን ለክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በቅጅ የሚልኩ ቢሆንም ለባለስልጣኑ እነዚህን መረጃዎች እንደማይልኩ ገልጸዋል፡፡

156. የባለስልጣኑ የቅርስ ኢንቬንቶሪ፣ ቁጥጥርና ደረጃ ማውጣት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ካለው የፌደራሊዝም የአሠራር ሂደት አንፃር ባለስልጣኑ ክልል ድረስ ወርዶ የቅርስ መረጃ አያያዝ በምን መልክ እንደሚከናወን ለማየት አለመቻሉን፤ ሆኖም በቅርስ ዙሪያ ያለው የመረጃ አያያዝ የተጠናከረና ወጥነት ያለው አለመሆኑን፣ በተወሰነ ደረጃ ክልሎች ቅርሶችን በሚመዘግቡበት ጊዜ በቅጅ ለባለሥልጣኑ የሚልኩበት ሁኔታ መኖሩን እና ባለስልጣኑ ይህንን ችግር ለመፍታት የተለያየ አውደ ጥናት አዘጋጅቶ ክልሎችን ለማስተማር ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ይህ ለመደረጉ በተግባር የታየ ነገር የለም ፡፡

157. ባለስልጣን መ/ቤቱ በቅርስ ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ወጥ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ያለማድረጉ ቅርሶች በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለማወቅ እንዳይችል የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ አስፈላጊ እገዛ በወቅቱ ለመስጠት እንዳይችል ያደርግዋል፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

158. የቅርስ አመዘጋገብ ተግባር የቅርስ አመዘጋገብ መስፈርትን በተከተለ እና ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ እየተከናወነ አለመሆኑ በሀገሪቱ ያሉ ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች ብዛት፣ አይነት እና ስርጭት ሁኔታ እንዳይታወቅ አድርጓል፡፡ የማይዳሰሱ ባሕላዊ ቅርሶች መመዝገብ አለመቻላቸው ከዓለማቀፋዊነት (globalization) ተጽዕኖ ጋር በተያያዙ ሁኔታም በማይዳሰሱ (intangable) ቅርሶች ላይ እየደረሰ ያለውን ጉዳት ለመቋቋም እንዳይቻል ያደርጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአርኪዮሎጂ ጥናት ሊከናወንባቸው የሚገቡ ቦታዎችን ሙሉ በሙሉ በሽፈነ መልኩ የማይከናወን መሆኑ ሀገሪቷ ያላትን የአርኪዮሎጂ ሀብት በአግባቡ እንድትጠቀም ለማድረግ አያስችልም፡፡

159. ባለስልጣኑ ለቅርሶች ጥገና ለማድረግ ቅርሶቹን በሚያስተዳድሩ አካላት ለሚቀርብለት ጥያቄ ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት አለመቻሉ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡትን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመዝግበው የሚገኙ ቅርሶችን ለጉዳት እና ለብልሽት ይዳርጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቅርሶች ጥገና ደረጃውን ጠብቆ ለመከናወኑ ክትትል አለመደረጉ፤ ቅርስን የያዙ አብያተ ክርስቲያናት ቅርሱን በመጠበቁ ረገድ የአቅም ውስንነት እየታየ መምጣቱ፣ ቅርሶችን በአግባቡ ለማስቀመጥ እና ለመጠበቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ሙዝየሞች በስፋት የሚገነቡበት ሁኔታ አለመኖር እና ደረጃውን በጠበቀ መልኩ አለመደራጀት ቅርሶችን በአግባቡ ለመጠበቅ የሚያስችል ሁኔታ አለመመቻቸቱን ያሳያል፡፡

160. ለቅርስ ቦታዎች አስተዳደር ሰነድ (site management plan) አለመኖር እና ከቅርስ ጥናትና ምርምር የሚገኝ ገቢ ለቅርሶቹ ጥበቃ፤ ጥገናና ልማት አለመዋል በተለይም በዓለም አቀፍ ቅርስነት ተመዝግበው የሚገኙ ቅርሶችን ከዓለም ቅርስነት ሊሠረዙ የሚችሉበትን ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል፡፡

161. ማንኛውም የልማት ሥራ ከመካሄዱ በፊት በቅድሚያ የአካባቢ የስጋት ግምገማ (Enviromental impact assessment) በማከናወኑ ረገድ ባለሥልጣኑ ሊሳተፍ

የሚችልበት ሁኔታ በግልጽ አለመቀመጡ፤ የቅርስ የደረጃ ምደባ ደንብ ፀድቆ አለመውጣቱ እና የቅርሶች ደረጃ አለመለየቱ እንዲሁም የቅርስ ጥናት እና ጥበቃ ባለድርሻ የሆኑ አካላት ሊኖራቸው የሚገባውን የሥራ ድርሻ እንዲለይ ተደርጎ እንዲያውቁት በማድረግ ቅርስን በተመለከተ የሥልጠና እና የሙያ ድጋፍ በቅርበት መስጠት አለመቻሉ በቅርሶች ላይ እየደረሰ ያለውን ጥፋት በተሻለ ብቃት ለመከላከል እና ለማቃለል ባለ ድርሻ አካላት የበኩላቸውን እንዳይወጡ ያደርጋል፡፡

162. በሀገር አቀፍ ደረጃ የተደራጀ የቅርስ መረጃዎችን በብቃት ለመለዋወጥ የሚያስችል የድረ-ገፅ አለመኖር ቅርሶችን በአግባቡ መዝግቦ ለመያዝ፣ ለመጠበቅ እና ለማስተዋወቅ፣ ቅርስ ነክ መረጃዎችን ለሚፈልጉ አካላት የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ወጥ የሆነ የመረጃ ለመለዋወጥ፣ ቅርሶች በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለማወቅ እንዳይችል የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ አስፈላጊ እገዛ በወቅቱ ለመስጠት እንዳይችል ያደርግዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

163. ባለሥልጣኑ የቅርስ መመዝገቢያ መመሪያዎችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን እና የመመሪያው ተጠቃሚ የሆኑ የባለድርሻ አካላትን አስተያየት በማካተት አዘጋጅቶ መመሪያውን ወቅታዊ የሚደረግበት ሁኔታ ሊያመቻች አጠቃቀሙንም በተመለከተ የተለያዩ የማስተዋወቂያ ዐውደ ጥናቶች በማዘጋጀት መመሪያውን ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ማድረግ ይገባዋል፡፡ ባለድርሻ አካላትም መመሪያውን በአግባቡ ተግባራዊ እያደረጉ መሆናቸው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

164. የሀገሪቱን ቅርሶች በብዛት፣ በአይነት ለይቶ የመመዝገቡ ተግባርም ሆነ ተገቢውን ጥበቃ እና እንክብካቤ የማድረጉን ተግባር የተሻለ እና ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል ክልሎች በቅርስ አመዘጋገብ ላይ ያላቸው ኃላፊነት በግልፅ ሊቀመጥ፣ ባለስልጣኑ ቅርስን በተመለከተ የሚያወጣውን መመሪያ የባህል እና ቱሪዝም ሚኒስቴርም ሆነ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት በአፋጣኝ የሚያፀድቁበት ሁኔታ ሊመቻች እና ክልሎች በቅርስ ምዝገባ ዙሪያ በሚያከናውኗቸው ሥራዎች ላይ ባለሥልጣኑ በእቅድ እና ወጥነት ባለው መልኩ አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያደርግበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

165. ቅርሶች ከመጥፋት በመጠበቅ ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ የሚቻልበትን ሁኔታ የተሻለ ለማድረግ እና ተገቢ የቅርስ መረጃ እንዲያዝ አመቺ የሆነ ሁኔታ ለመፍጠር በሀገሪቱ ያሉ የማይዳሰሱ (intangible) ቅርሶች ሙሉ ለሙሉ ለመመዝገብ ከፍተኛ ቅንጅት እና ሀብት የሚጠይቅ ከመሆኑ አንፃር ባለሥልጣኑ ከሚያከናውነው ተግባር በተጨማሪ ክልሎች በእነዚህ የማይዳሰሱ (intangible) ቅርሶች አመዘጋገብ ላይ ለመሳተፍ የሚያስችላቸው ሁኔታ ሊመቻች፤ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀው የማይዳሰሱ (intangible) ቅርሶች መመዝገቢያ መመሪያው የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ በየጊዜው የሚሻሻልበትና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲደርስ በማድረግ የማይዳሰሱ (intangable) ቅርሶች ምዝገባ በተሻለ ሁኔታ

የሚካሄድበት መንገድ ቢመቻች፣ የቅርስ ምዝገባ የሚያከናውኑ ባለሙያዎች ስለሚመዘገበው ቅርስ በቂ ዕውቀት እና መረጃ እንዲኖራቸው ተገቢው ድጋፍ እና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

166. በሀገሪቷ የአርኪዮሎጂ ጥናት ሊከናወንባቸው የሚገቡ ቦታዎችን ባዳረሰ መልኩ ጥናት ለማድረግ የሚመጡ ባለሙያዎችንም በአግባቡ ለማስተናገድ፣ በአርኪዮሎጂ ቅርሶች ላይ የሚደርሰውን ጥፋት ለመከላከል እና ለመቀነስ ለአርኪዮሎጂ ጥናት የሚውሉ ቦታዎችን ለይቶ በመመዝገብ መረጃዎች የሚይዙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

167. ቅርሶች በሚጠገኑበት ወቅት በወጣው የቅርስ ጥገና መስፈርት መሠረት እንዲሆን እና የሀገሪቱን ውድ ቅርሶች ከጥፋት ለመታደግ የጎላ ሥራ ለማከናወን እንዲቻል ለቅርስ ጥገና የሚሆኑ ምርቶች የሀገሪቱን ማንነት የሚገልፁ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመዘገቡ ቅርሶች በሚገኙበት አካባቢ የሚገኙበት ሁኔታ ለማመቻቸት በየደረጃው ከሚገኙ የኢንቨስትመንት መ/ቤቶች ጋር የውይይት መድረክ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

168. የላብራቶሪ አጠቃቀምን እንዲሁም የቅርሶች ውሰት፣ ማሰባሰብ እና ማስወገድ ተግባራትን በተቀላጠፈ እና ሥርዓትን በጠበቀ ሁኔታ ለማከናወን እንዲቻል አስፈላጊ መመሪያዎች እና ፖሊሲዎች በሚመለከተው አካላት ሊጸድቁ የሚችሉበት ሁኔታ እንዲመቻች ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

169. በቅርሶች ላይ እየደረሰ ያለውን ጥፋት ለመከላከል እና ለመቀነስ እንዲችል የቅርስ ባለሙያዎችን በሚፈለገው መጠን ለማፍራት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በቅርበት ሊሠራ፣ የቅርስ ጥገና ሙያተኞች እውቅናና ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ ሊመቻች እንዲሁም ባለስልጣኑ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ፈቃድ ሳይሰጥ ጥገናዎች እንዳይደረጉ ከቅርሱ ባለቤቶች ጋር የተሻለ ግኑኝነት በመፍጠር ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

170. በቅርሶች ላይ እየደረሰ ያለውን ጥፋት ለመቀነስ ባለስልጣኑ በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር እና በማቀናጀት ቅርስን የመጠገን አቅማቸውን በማጎልበት በየአካባቢያቸው የሚገኙ ቅርሶችን እንዲጠግኑ እውቅና እና ፈቃድ የመስጠት ተግባርን ማጥናት የሚገባ ሲሆን፣ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ

ከተደረገላቸው በኋላ ለቅርሱ ጥገና እንክብካቤ በተቀመጠው የቅርስ ጥገና ደረጃ (standard) መሠረት ለመከናወኑ ለመከታተል እና ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

171. በቅርሶች ላይ እየደረሰ ያለውን ጥፋት በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ ለቅርስ ባለቤቶች በቅርሶች ላይ ያላቸውን የአጠባበቅ ግንዛቤ እንዲዳብር ስልጠና መስጠት፣ ቅርስን በባለቤትነት የያዙ አብያተ ክርስቲያናት ቅርሱን በመጠበቁ ረገድ ለሚታይባቸው የአቅም ውስንነት ለማቃለል እንዲቻል በቅርበት ድጋፍ ሊደረግ፤ ቅርሶች ባሉበት አካባቢ በአግባቡ ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሙዝየሞች እንዲደራጁ፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተለይ በጣም ውድ ቅርስ የያዙ ሙዝየሞች በጥናት ተለይተው ለጉብኝት ክፍት በሚሆኑበት ወቅት ተገቢው ጥበቃ የሚደረግበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

172. በዓለም አቀፍ ቅርስነት የተመዘገቡ የኢትዮጵያ ቅርሶች በቅርስነታቸው ለማቆየት የቅርስ ቦታዎች አስተዳደር ሰነድ (heritage management plan) እንደ አንድ ዋነኛ መስፈርት የሚታይ በመሆኑ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት እና የቅርስ ቦታዎች አስተዳደር ሰነድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

173. የሀገሪቱ ውድ ቅርሶች አለአግባብ ከሀገር ውጪ እንዳይወጡ እና ለንግድ እንዳይውሉ የንግድ ተቋማት የንግድ ፈቃድ በሚያወጡበት ወቅት በንግድ ሚኒስቴር እና በቅርስ ጥናት እና ጥበቃ ባለሥልጣን መካከል ቀጥተኛና ወጥ የሆነ ግንኙነት መፍጠር ይኖርበታል፡፡

174. በአርኪዮሎጂ ቦታዎች ላይ የሚደረገው ቁጥጥር የተሻለ እንዲሆን በቅርስ ቦታዎች ላይ ጥናት እና ምርምር ከሚያደርጉ ቡድኖች ጋር ከባለሥልጣኑ ለክትትል የሚመደብ ባለሙያ (Antiquity Officer) ከሙያው ጋር የተያያዘ ልምድ እና እውቀት ያላቸው መሆን ይገባቸዋል፡፡ ለነዚህ ባለሙያዎች ቀጣይነት ያለው የሥልጠና ዕቅድ ተይዞ ስልጠና የሚሰጥበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

175. ለቅርሶች ጥበቃ፣ እንክብካቤ እና ልማት ይረዳ ዘንድ በአርኪዮሎጂ ቦታዎች ላይ ከሚከናወኑ የጥናት ሥራዎች የጥናት ፕሮጀክቱን ዋጋ መሠረት በማድረግ ከሚገኘው አስር በመቶ (10%) ገቢ ላይ ግማሹ (50%) ጥናቱ ለተደረገበት

የፌዴራልም ሆነ የክልል ቅርሶች ጥበቃ እና እንክብካቤ ብቻ የሚውልበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

176. ባለሥልጣኑ የሚታይበትን የአቅም ውስንነትን ለማቃለል እና በቅርሶች ላይ እየደረሰ ያለውን ጥፋትና ምዝበራ ለማስወገድ እና ለማቃለል የቅርስ ጥናት እና ጥበቃ ተግባር የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሊኖራቸው የሚገባውን የሥራ ድርሻ በጥናት በመለየት እንዲያውቁት ሊያደርግ እና ድርሻቸውን ሊወጡ የሚችሉበት ሁኔታን ሊያመቻች ይገባል፡፡

177. ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ወጥነት ያለው መርሐ ግብር ነድፎ በመንቀሳቀስ በቅርስ ላይ ጥፋት የሚያደርሱ አካላት ተገቢው የቅጣት ውሳኔ በባለስልጣኑ መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 209/92 አንቀፅ 45 ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ በተቀመጠው መሠረት እንዲያገኙ ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

178. በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ስር ያሉ መ/ቤቶች ከባለሥልጣኑ ጋር ለጋራ ዓላማ በተቀናጀ መልኩ አብሮ የሚሰሩበት መንገድ ሊፈጠር ይገባል፡፡

179. በቅርስ ዙሪያ ያሉ ተግባራትን የሚያከናውኑ ባለሙያዎች ክህሎት እንዲዳብር እና በየደረጃው ብቃት ያለው ባለሙያ እንዲኖር ለማድረግ በቅርስ አጠባበቅ፣ ጥገና እና እንክብካቤ ዙሪያ የሚሰጠው ሥልጠና ወጥ በሆነ መልኩ ክልል፤ ዞን እና ወረዳ ድረስ በማውረድ ሊሰጥ ይገባል፡፡ እንዲሁም በቅርስ ጥናት ኤክስፐርቶች የሚደረጉ ጥናቶች ላይ በየክልሉ የሚገኙ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ልምድ እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡

180. በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻ አካላት ቅርስን በተመለከተ የሚጠበቅባቸውን ተግባር በአግባቡ እንዲወጡ ለማድረግ ባለስልጣኑ አዘጋጅቶ ያቀረበው የቅርስ ደረጃ ምደባ ደንብ በሚመለከተው አካል ፀድቆ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተሰራጭቶ ተግባራዊ የሚሆንበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

181. የሀገሪቱ ቅርሶች በየደረጃው ባሉ ባለድርሻ አካላት በአግባቡ ተመዝግበው፣ ተጠብቀው እና እንክብካቤ ተደርጎላቸው ለልማት የሚውሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር ለማድረግ የባለስልጣኑ እና የክልሎች አዋጅ በተጣጣመ መልኩ እንዲዘጋጅ እንዲሁም

ባለስልጣኑ እና  የክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ግልፅና ወጥነት ያለው የሥራ ድርሻ እንዲኖራቸው በግልጽ ተለይቶ እንዲቀመጥ ሊደረግ ያደርጋል፡፡

182. በተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶች ትግበራ ወቅት በቅርሶች ላይ ሊደርስ የሚችል አደጋን ለመቀነስ የቅርስ ማዳን ጥናት (Impact assessment) ከሚመለከታቸው ሌሎች ባለድርሻ መ/ቤቶች እና አካላት ጋር ባለስልጣኑ ሊሠራ የሚችልበት የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ  ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

183. የቅርሰ ጥበቃ ጥገናና እንክብካቤ  ሥራ ላይ ከፍተኛ የሙያ ስነምግባር  እውቀትና ልምድ ያለው ባለሙያ ለማፍራት እንዲቻል የቅርሰ ጥበቃ ጥገናና እንክብካቤ  ጽንሰ ሃሳቦች በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት እርከኖች የትምህርት ሥርዓት ውስጥ እንዲካተቱ እና በዚህ ሙያ ብቃት እና ሥነምግባር ያላቸው ባለሙያዎች ሊፈሩ የሚችሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

184. በቅርስ ዙሪያ የሚደረጉ የመረጃ ልውውጦች ቀልጣፋና ዘመናዊ እንዲሆኑ ባለስልጣኑ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሁሉም ክልሎች በመረጃ መረብ የሚገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

185. በሀገሪቱ የሚገኙ እና የተመዘገቡ ቅርሶችን በአግባቡ ለመጠበቅ፣ ለህብረተሰቡ ለማስተዋወቅ እና ቅርስ ነክ መረጃዎችን ለሚፈልጉ አካላት የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር እና በመቀናጀት የቅርሶችን መረጃ በህትመት፤ በፖስተር፤ በመጽሄት፤ በመረጃ መረብና በሌሎች የመገናኛ መንገዶች ማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት ሊዘርጋ ይገባል፡፡

በመጨረሻም ባለሥልጣኑ እንዲሁም በፌዴራል እና በክልል የሚገኙ ባለድርሻ አካላት እና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

## I. በባለስልጣኑ የሚከናወነው የቅርስ ምዝገባ፤ ጥበቃና እንክብካቤ በብቃትና በቁጠባ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም፤

1. ቅርሶች እንዲጠበቁ ባለስልጣኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የአመዘጋገብ መመሪያ ሊኖረው ይገባል፡፡
2. ተንቀሳቃሽና ቋሚ ቅርሶች በሚገኙበት ቦታ በብዛት እና በአይነት ተለይተው ምዝገባ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡
3. ባህላዊና ታሪካዊ የማይዳሰሱ ቅርሶች በብዛት በአይነትና በስርጭት ተለይተው በሀገር አቀፍ ደረጃ መመዝገብ አለባቸው፡፡
4. የቅርስን ምዝገባ የሚያደርጉ ባለሙያዎች ሙያው የሚጠይቀውን ክህሎትና ስነምግባር የሚያሟሉ ሊሆኑ ይገባል፡፡
5. ባለስልጣኑ ለአርኪዮሎጂ ጥናት የሚውሉ ቦታዎችን ለይቶ ምዝገባ ማድረግ አለበት፡፡
6. የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ስራ ራሱን የቻለ መስፈርት (ስታንዳርድ) ሊኖረው እና ምዝገባውም መስፈርቱን በጠበቀ መልኩ መከናወን ይገባዋል፡፡
7. የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን በቅርስ ጥገና እና እንክብካቤ ዙሪያ በተገልጋዮች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡
8. የቅርስ ላቦራቶሪ አጠቃቀም እና በአለም አቀፍና በአገር ውስጥ ባሉ ሙዚየሞች መካከል የሚደረግ የቅርስ ውሰት መመሪያዎች እንዲሁም የቅርስ ማስወገድና ማሰባሰብ ፖሊሲዎች ሊዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡
9. ከባለስልጣን መ/ቤቱ ዕውቅና እና ፈቃድ ውጭ በቅርሶች ላይ ጥገናና እንክብካቤ እንዳይደረግ ተገቢው ቁጥጥር እና ክትትል መደረግ አለበት፡፡
10. የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ለቅርስ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት በቅርስ አጠባበቅ ዙሪያ ለሚቀርብለት ጥያቄ ወቅታዊ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡
11. ባለስልጣኑ ለሚጠብቃቸው ቅርሶች የቅርስ አስተዳደር ሰነድ (Heritage management plan) ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
12. በስጦታ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄዱ እቃዎች ቅርስ አለመሆናቸው የሚረጋገጥበት እና ቅርሶች ለንግድ ዓላማ እንዳይውሉ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
13. የቅርስ ጥናት ከሚያደርጉ አካላት ጋር ከባለስልጣኑ የሚላኩ ባለሙያዎች ለመምረጥ የሚያስችል የመምረጫ መስፈርት ሊኖር ይገባል፡፡
14. ባለስልጣኑ ከቅርስ ጥናትና ምርምር ባለሙያዎች የጥናት ሥራ በፕሮጀክቱ ዋጋ

ተመን መሠረት የሚገኘው አስር በመቶ (10%) ገቢ ለቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ማዋል አለበት::

15. ቅርሶችን ከምዝበራና ከጥፋት ለመጠበቅ ባለስልጣኑ መ/ቤት እና በፌዴራል ደረጃ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ማንነት እና ሊኖራቸው የሚገባውን የሥራ ድርሻ በጥናት ሊለይ እና ባለድርሻ አካላቱ እንዲያውቁት ሊያደረግ ይገባል፡፡

## II. <u>የቅርስ ጥናትና ጥበቃን በተመለከተ የማመለከታቸው ሌሎት ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱንና በብቃት ተግባራዉ መሆኑን መገምገም፤</u>

16. በቅርስ አመዘጋገብ አጠባበቅና ጥገና ዙሪያ ባለሥልጣኑ እና ክልሎች ያላቸው የሥራ ድርሻ በግልጽ መቀመጥ አለበት፡፡
17. ቅርሶችን ከምዝበራና ከጥፋት ለመጠበቅ ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበትን እቅድ በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
18. ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተጠሪ ከሆኑ መ/ቤቶች ጋር በጋራ ሊሰሩ የሚገባቸውን ሥራዎች በተቀናጀ ሁኔታ ለመሥራት የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
19. ባለስልጣኑ ለክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች በየደረጃው በቅርሶች ዙሪያ ለሚደረጉ ማንኛውም ስራዎች የሙያ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡
20. የሀገሪቱን ቅርሶች በአግባቡ ለማስተዳደር እና ለመጠበቅ በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ሊተዳደሩና ሊጠበቁ የሚገባቸውን ቅርሶች ደረጃ ሊወጣ ይገባል፡፡
21. የልማት ሥራ ሲከናወን በቅርስ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ባለሥልጣኑ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የማዳን ሥራ ማከናወን አለበት፡፡
22. በቅርስ ጥበቃ፣ ጥገናና እንክብካቤ ሥራ ላይ ለሚመደቡ ሠራተኞች ከሀገሪቱ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ የሥነ-ምግባር ደንብ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
23. የተመዘገቡ ተንቀሳቃሽ ቋሚ ቅርሶችን መረጃ በአግባቡ ሊይዝ ይገባል፡፡
24. በባለሥልጣኑ የሚከናወን የቅርስ ምዝገባ ስራ በማዕከል በዳታ ቤዝ ተይዞ ከክልሎች ጋር በኔትወርክ የተገናኘ እና መረጃዎችን በቀላሉ ለመለዋወጥ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡
25. የተለያዩ የቅርስ መረጃዎችን በድረ-ገጽ፤ በህትመት፤ በፖስተር፤ በመፅሄትና በሌሎች አመቺ መንገዶች ማሰራጨት የሚያስችለውን ስርዓት መዘርጋት አለበት፡፡
26. በቅርሶች ዙሪያ ለሚከናወኑ ሥራዎች በሁሉም ባለድርሻ አካላትና በባለሥልጣኑ መካከል የመረጃዎች ልውውጥ ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡